# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የአትሌቲክስ ስፖርትን በአገሪቱ በማስፋፋት ብቃት ያላቸውን አትሌቶች ለማፍራት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በተመለከተ የተከናወነ
## የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መስከረም/2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


**መግቢያ ........ 1**

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አመሠራረት፤ ........ 1
የፌዴሬሽኑ ዓላማ፤ ........ 2
የፌዴሬሽኑ ሥልጣን እና ተግባር፤ ........ 3
የፌዴሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል፤ ........ 3
የፌዴሬሽኑ የፋይናንስ ምንጭ፤ ........ 4

**የኦዲቱ ዓላማ ........ 5**

**የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች፤ ........ 5**

**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፤ ........ 6**

**የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ፤ ........ 6**

**የኦዲት ግኝቶች ........ 7**

**I. በሀገሪቱ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት አጥጋቢና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ........ 7**

1.1 የአትሌቲክስ ስፖርትን በሀገር አቀፍ ደረጃ በማስፋፋት ብቁ እና ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት የተዘረጋው አሠራር አጥጋቢና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥን በተመለከተ፣ ........ 7
*የአትሌቲክስ ስፖርትን በኃላፊነት የሚያንቀሳቅሱ አካላት አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሠራርን በተመለከተ፤ ........ 7*
*የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የሚያስፈልጉ ደንቦችና መመሪያዎችን በተመለከተ፤ ........ 8*
*የፋይናንስ ድጋፍ ማሰባሰብን በተመለከተ፤ ........ 9*
*ዝቅተኛ ተሳትፎ እና ውጤት የሚታይባቸው የአትሌቲክስ ስፖርት ውድድር መስኮችን በተመለከተ ........ 11*

1.2. በሀገሪቱ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የተዘረጋው የሥልጠናና የውድድር ሥርዓት ግልጽ፤ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ........ 12
*በብሔራዊ አትሌትነት የሚታቀፉ አትሌቶች ምርጫ በተመለከተ፣ ........ 12*
*ሀገርን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶች ምርጫን በተመለከተ ........ 13*
*ብሔራዊ ቡድኑን የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞች ምርጫን በተመለከተ ........ 14*
*የአሠልጣኝነት እና የዳኝነት ኮርሶች ሥልጠና የሚሰጡ አሰልጣኞች እና ሰልጣኞችን በተመለከተ፤ ........ 15*
*በአሰልጣኝነትና የዳኝነት ኮርስ ስልጠና ላይ የሚካፈሉ ሠልጣኞች ብዛትን በተመለከተ፤ ........ 16*
*ለሠልጣኞች የሚሰጥ ፈተና ዝግጅትና ግምገማን በተመለከተ፤ ........ 16*
*የአሰልጣኝነት እና የዳኝነት ስልጠና ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትን በተመለከተ ........ 17*
*የሥልጠና ማቴሪያል ዝግጅትን በተመለከተ ........ 18*
*የሥልጠና መርሐ ግብር ዝግጅትን በተመለከተ ........ 18*
*በፌዴሬሽኑ ስር አትሌቶችን የሚያሠለጥኑ አሠልጣኞች ግምገማን በተመለከተ ........ 19*
*የአትሌቲክስ ስፖርት አሠልጣኝነት የሙያ ፈቃድ ደረጃን በተመለከተ ........ 19*
*ውድድር ማካሄጃ መሳሪያዎችን በተመለከተ ........ 20*
የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት አቀራረጽን በተመለከተ፤ ........ 20
በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች ላይ የሚደረግ ክትትልና ግምገማን በተመለከተ፤ ........ 21
ለታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች የሚደረግ ድጋፍን በተመለከተ፤ ........ 22
በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት የሚታቀፉ ታዳጊ ወጣቶች አመራረጥን በተመለከተ፤ ........ 22
በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት የታቀፉ ታዳጊ ሠልጣኞች ከፕሮጀክቱ የሚለቁበትን ጊዜ በተመለከተ፤ ........ 23
በታዳጊ አትሌቲክስ ፕሮጀክት የታቀፉ ሠልጣኞች የስልጠና ጊዜን በተመለከተ፤ ........ 23
የታዳጊ ወጣቶች ስልጠና አሰጣጥ መመሪያን በተመለከተ፤ ........ 24
ለታዳጊ የአትሌቲክስ ሰልጣኞች መሰጠት ያለበትን የሕክምና አገልግሎት በተመለከተ፤ ........ 25
በታዳጊ አትሌቶች ውድድር ላይ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ፤ ........ 26
*አትሌት ማናጀሮች ፈቃድ አሠጣጥ እና ክትትልን በተመከተ ........ 26*
*በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ የሴቶች ተሳትፎን በተመለከተ፤ ........ 27*
*የጸረ ዶፒንግ/አበረታች መድሐኒቶች/ ስምምነትን ተግባራዊ ማድርግን በተመለከተ ........ 27*

*በውጭ ሀገራት በግል ውድድር ለማድረግ የሚጠይቁ አትሌቶች ፈቃድ አሠጣጥን በተመለከተ* ........ 28
*ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌላቸው አትሌቶች በሀገር ውስጥ ልምምድ እንዲያደርጉ ፈቃድ መስጠትን በተመለከተ፤* ........ 30
*ክሶች እና አቤቱታዎችን ገለልተኛ በሆነ አካል ማስተናገድን በተመለከተ፤* ........ 30
*የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦች አደረጃጀትን የሚመለከት መመሪያ ማዘጋጀትን በተመለከተ* ........ 31

**II. በፌዴራሽኑ የአትሌቲክስ ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ፣ አጠባበቅ፣ አጠቃቀምና ልውውጥ አጥጋቢ እና አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ ........ 32**

*ፌዴሬሽኑን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ በተመለከተ* ........ 32
*አትሌቲክስን የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎችን ለተጠቃሚ አካላት ማሠራጨትን በተመለከተ፤* ........ 33

**III. የአትሌቲክስ ስፖርትን በብቃት ለማከናወን እንዲቻል በፌዴሬሽኑ የሚከናወኑ የአቅም ግንባታ እንቅስቃሴዎች አጥጋቢነትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ ........ 35**

*የአትሌቲክ ማሰልጠኛ ማዕከላት ግንባታን እና አስፈላጊው ቁሳሱስ መሟላትን በተመለከተ፤* ........ 35
*የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በተመለከተ፤* ........ 36
*ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ መንደር ግንባታን በተመለከተ፤* ........ 37
*የአዲስ አበባ ስታዲየም የመሮጫ ትራክ አጠቃቀምን በተመለከተ፤* ........ 38

**የማሻሻያ ሀሳቦች ........ 39**

*የአትሌቲክስ ስፖርትን በኃላፊነት የሚያንቀሳቅሱ አካላት አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሠራርን በተመለከተ፤* ........ 39
*የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የሚያስፈልጉ ደንቦችና መመሪያዎችን በተመለከተ፤* ........ 39
*የፋይናንስ ድጋፍ ማሰባሰብን በተመለከተ፤* ........ 39
*ዝቅተኛ ተሳትፎ እና ውጤት የሚታይባቸው የአትሌቲክስ ስፖርት ውድድር መስኮችን በተመለከተ* ........ 40
*በብሔራዊ አትሌትነት የሚታቀፉ አትሌቶች ምርጫን በተመለከተ፣* ........ 40
*ሀገሪቱን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶች ምርጫን በተመለከተ* ........ 41
*ብሔራዊ ቡድኑን የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞች ምርጫን በተመለከተ* ........ 41
*የአሠልጣኝነት እና የዳኝነት ኮርሶች ሥልጠና የሚሰጡ አሰልጣኞች እና ሰልጣኞችን በተመለከተ፤* ........ 41
*በአሰልጣኝነትና የዳኝነት ኮርስ ስልጠና ላይ የሚካፈሉ ሠልጣኞች ብዛትን በተመለከተ፤* ........ 42
*ለሠልጣኞች የሚሰጥ ፈተና ዝግጅትና ግምገማን በተመለከተ፤* ........ 42
*የስልጠና መርሐ ግብር ዝግጅትን በተመለከተ፤* ........ 43
*በፌዴሬሽኑ ስር አትሌቶችን የሚያሠለጥኑ አሠልጣኞችን ግምገማን በተመለከተ* ........ 43
*የአትሌቲክስ ስፖርት አሠልጣኝነት የሙያ ፈቃድ ደረጃን በተመለከተ* ........ 43
*ውድድር ማካሄጃ መሳሪያዎችን በተመለከተ፤* ........ 44
*የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት አቀራረጽን በተመለከተ፤* ........ 44
*በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች ላይ የሚደረግ ክትትልና ግምገማን በተመለከተ፤* ........ 44
*ለታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት የሚደረግ ድጋፍን በተመለከተ፤* ........ 44
*በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት የሚታቀፉ ታዳጊ ወጣቶች አመራረጥን በተመለከተ፤* ........ 45
*በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት የታቀፉ ታዳጊ ሰልጣኞች ከፕሮጀክቱ የሚለቁበትን ጊዜ በተመለከተ፤* ........ 45
*የታዳጊ ሠልጣኞች የስልጠና ጊዜን በተመለከተ፤* ........ 45
*የታዳጊ ወጣቶች ስልጠና አሰጣጥ መመሪያን በተመለከተ፤* ........ 45
*ለታዳጊ የአትሌቲክስ ሰልጣኞች መሰጠት ያለበትን የሕክምና አገልግሎት በተመለከተ፤* ........ 46
*በታዳጊ አትሌቶች ውድድር ላይ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ፤* ........ 46
*አትሌት ማናጀሮች ፈቃድ አሠጣጥ እና ክትትልን በተመከተ* ........ 46
*በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ የሴቶች ተሳትፎን በተመለከተ፤* ........ 46
*የጸረ ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ ስምምነትን ተግባራዊ ማድርግን በተመለከተ* ........ 47
*በውጭ ሀገራት በግል ውድድር ለማድረግ የሚጠይቁ አትሌቶች ፈቃድ አሠጣጥን በተመለከተ* ........ 47
*ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌላቸው አትሌቶች በሀገር ውስጥ ልምምድ እንዲያደርጉ ፈቃድ መስጠትን በተመለከተ፤* ........ 48
*ክሶች እና አቤቱታዎችን ገለልተኛ በሆነ አካል ማስተናገድን በተመለከተ፤* ........ 48
*የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦችን አደረጃጀት የሚመለከት መመሪያ ማዘጋጀትን በተመለከተ* ........ 48
*ፌዴሬሽኑን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ በተመለከተ* ........ 48
*አትሌቲክስን የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎችን ለተጠቃሚ አካላት ማሠራጨትን በተመለከተ፤* ........ 49
*የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከላት ግንባታ እና በአስፈላጊው ቁሳቁስ መሟላትን በተመለከተ* ........ 49

**የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን በተመለከተ፤** ........ 49
**ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ መንደር ግንባታን በተመለከተ፤** ........ 49
**የአዲስ አበባ ስታዲየም የመሮጫ ትራክ አጠቃቀምን በተመለከተ፤** ........ 50

**አባሪዎች** ........ **I**

**ጠቅለላ ጉባኤው ተሳታፊዎች** ........ I
**የኦዲት መስፈርቶች** (EVALUATIVE CRITERIA) ........ II

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. አካላዊ፣ አዕምሮአዊ እና ማኅበረሰባዊ ጤንነቱ የተጠበቀ፣ በጋራ የመስራት ባህልን ያዳበረ እና የዓላማ ጽናት ያለው ኅብረተሰብን መገንባት የስፖርት መሠረታዊ ዓላማ ከመሆኑም በላይ አርዓያ ሊሆኑ የሚችሉ ዜጎችን በማፍራትም ቀጣዩ ትውልድ ከመጥፎ እና አላስፈላጊ ተግባራት ተለይቶ እንዲያድግ ስፖርት የጎላ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በመሆኑም ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች የተለያዩ ስፖርት እንቅስቃሴ አይነቶች ተካፋይ የሚሆኑበትን ሁኔታ በማመቻቸት የዕድሉ ተጠቃሚ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው፡፡

2. በዓለምም ሆነ በሀገራችን በጣም ተወዳጅ እና ተዘውታሪ ከሆኑት ስፖርቶች መካከል በ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው አጋማሽ መገባደጃ ላይ በሀገራችን የተጀመረው የአትሌቲክስ ስፖርት አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ይህ ስፖርት በሀገሪቱ እንዲስፋፋ ጥረት መደረጉን እና በአሁኑ ወቅትም ሀገራችን በዚህ ስፖርት በዓለም አቀፍ ደረጃ እየታወቀችበት እንደመጣች ይታወቃል፡፡

## የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አመሠራረት፤

3. በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ በሀገራችን የተደራጁ ክለቦች እና ማህበሮች በስፋት ከመቋቋማቸው በፊት በተወሰኑ የአትሌቲክስ ዘርፎች (events) ብቻ በጥቂት መንግስታዊ ተቋማት ማለትም በጦር ሠራዊት፣ በፖሊስ ሠራዊት፣ በአየር ኃይል እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ መጠነኛ እንቅስቃሴ ይከናወን እንደነበር በሀገሪቱ የአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ የተጠናቀሩ እና የተገኙ መረጃዎች ያስረዳሉ:: የአትሌቲክስ ስፖርት እንቅስቃሴን በበላይነት እንዲመራ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በ1941 ዓ.ም. ተመስርቷል፡፡ የአትሌቲክስ ስፖርት አይነቶች በዘመናዊ መልክ መዘውተር እና ሀገሪቱን በመወከልም በዓለም አቀፍ ውድድርም መሳተፍ የተጀመረው ግን ከሰባት ዓመታት በኋላ በ1948 ከሜልቦርን ኦሎምፒክ ወዲህ ነው፡፡ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በ1953 ዓ.ም. የዓለም አቀፍ አማተር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አባል የሆነ ሲሆን፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሀገሪቱ በአዘጋጅ

አገሮች እየተጋበዘች የተለያዩ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍአዊ ውድድሮች ትካፈል እንደነበር ከተገኙት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል::

4. ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ የአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ ያላትን ተሳትፎ ለማጠናከር በ1979 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በመተባበር በፓይለት ፕሮጀክት ስም የማራቶንና የግማሽ ማራቶን ሠልጣኞችን በማቀፍ በአራት ክፍለ ሀገሮች የአትሌቲክስ ሥልጠና መስጠት የተጀመረ ሲሆን፣ በ1993 ዓ.ም. ደግሞ ተተኪ አትሌቶች በቀጣይነት ለማፍራት እንዲያስችል በሚል ዓላማ በአማራ፤ በትግራይ፤ በደቡብና በኦሮሚያ ክልሎች ቀደም ሲል ብቃት ያላቸው አትሌቶች የወጡባቸውን ቦታዎች ቅድሚያ በመስጠት አምስት አምስት የፕሮጀክት ጣቢያዎች በመክፈት ዳጊ ወጣቶች በአትሌቲክሱ ዙሪያ ልምድ ንዲያገኙ ጥረት መደረጉ ታውቋል:: ከዚህ በተጨማሪ በ1996 ዓ.ም. የፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባኤ ተስፋ የሚጣልባቸውን ወጣት አትሌቶች ተቀብለው የሚያሰለጥኑ ማሰልጠኛ ማዕከላት በአራት ክልሎች ማለትም በአማራ፤ በትግራይ፤ በኦሮሚያ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች ንዲቋቋሙ በተላለፈው ውሳኔ መሠረት ማሰልጠኛ ማዕከላት እንዲገነቡ የተደረገ እና የተወሰኑት የማሠልጠን ተግባር የጀመሩ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል::

## <u>የፌዴሬሽኑ ዓላማ፤</u>

5. የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጥቅምት 2001 ዓ.ም. ተሻሽሎ በፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባኤው በጸደቀው የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚተዳደር ሲሆን፣ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ላይ የሚከተሉት አራት አበይት ዓላማዎች ተቀምጠዋል:: እነሱም:-

- የዘር፣ የፆ ፣ የጎሳ፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ እና የቀለም ልዩነትና መድልኦ ሳይኖር የአትሌቲክስ ስፖርት በኢትዮጵያ ንዲ ወቅ እና እንዲስፋፋ ማድረግ፣
- በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ የሚወጡትን ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ክፍለ አህጉራዊ ደንቦችና መመሪያዎች በአገሪቱ ንዲ ወቁ ማድረግና ማስፈጸም፣
- የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማሳደግና ለማስፋፋት የሚያስችል ግንኙነትና ትብብር መፍጠር፣
- የአትሌቲክስ ስፖርትን ተሳትፎ በመላው ሀገሪቱ እንዲስፋፋ ማድረግ

ናቸው::

## የፌዴሬሽኑ ሥልጣን እና ተግባር፤

6. የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በጠቅላላ ጉባኤው በጸደቀው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥቶ ል:: እነዚህም:-

- በስፖርት ፌዴሬሽኖች መቋቋሚያ መመሪያ እና በዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማ በር ህግና ደንብ መሠረት በአገሪቱ ውስጥ የአትሌቲክስ ስፖርትን ማሳደግና ማስፋፋት፤
- ደረጃቸውን የጠበቁ የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ማቋቋምና ማስፋፋት፤
- የተለያዩ አትሌቲክስ ነክ የሆኑ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማደራጀትና ማሰራጨት፤
- የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦች ንዲደራጁ መመሪያ የማውጣትና ተፈጻሚነቱን የመከ ተል፤
- የ ዳጊ ወጣቶችንና የሴቶችን የአትሌቲክስ ስፖርት ተሳትፎን ማሳደግ፤
- ምርጥ አትሌቶችን ለማፍራት የሚያስችል ዘመናዊ የሥልጠና ስልት መቀየስ፤
- ከዓለም አቀፍና ከሀገር ውስጥ የአትሌቲክስ ተቋማት ጋር በመተባበር በአትሌቲክስ ዙሪያ ኮርሶችን፣ ሴሚናሮችን፣ ወርክሾፖችን እና ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድርግ፤
- የአሰልጣኞችና የዳኞች መመልመያ መስፈርት እንዲሁም ደረጃ ማውጣትና ፈቃድ መስጠት፤
- የአትሌቲክስ ስፖርትን የሚመለከቱ ማናቸውም ክሶችና አቤቱ ዎች ላይ ውሳኔ መስጠት፤
- ኢትዮጵያ ያጸደቀችው የፀረ-ዶፒንግ ኮንቬሽን ማክበርና ማስከበር

የሚሉት ናቸው::

## የፌዴሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል፤

7. የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከፌዴራል እና ከክልል መ/ቤቶች እንዲሁም ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሚወከሉ ተሳታፊዎችን በሚያካትት ጠቅላላ ጉባኤው በበላይነት የሚመራ ሲሆን፤ በጠቅላላ ጉባኤው የተመረጠ የሥራ አሥኪያጅ ኮሚቴ የፌዴረሽኑን የዕለት ተዕለት ተግባራት

ያከናውናል፡፡ የፌዴሬሽኑ ሥራ አሥኪያጅ ኮሚቴ አንድ ኘሬዝዳንት፣ አንድ ምክትል ኘሬዝዳንት፣ አንድ ዓቃቤ ንዋይ፣ አራት አባላት እና ሁለት የአትሌቶች ተወካዮች እንዲኖሩት ተደርጎ የተዋቀረ ሲሆን፣ ለሥራ አሥኪያጅ ኮሚቴ ተጠሪ የሆነ አንድ የጽ/ቤት ላፊ አለው፡፡ ለጽ/ቤት ላፊው ተጠሪ የሆኑ የቴክኒክ፣ የሕዝብ ግንኙነት ና የአስተዳደርና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬቶች አሉት፡፡ በጠቅላላ ጉባኤው የሚወከሉ ተሳታፊዎች ዝርዝር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

8. ፌዴሬሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የሚተዳደረው በአማተርነት ተመርጠው በሚያገለግሉ ሠራተኞች ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በአጠቃላይ 17 ቋሚ እንዲሁም አራት ከወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር በውሰት የመጡ በድምሩ 21 ሠራተኞች አሉት፡፡ ከዚህ የሰው ኃይል በተጨማሪም ብሔራዊ የአትሌቲክስ ክለቡን የሚያሰለጥኑ 21 የስፖርት ባለሙያዎች በ2001 ዓ.ም በኮንትራት ተቀጥረው በመሥራት ላይ የሚገኙ መሆኑን ለማረጋጥ ተችሏል፡፡

## የፌዴሬሽኑ የፋይናንስ ምንጭ፤

9. የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሥራውን የሚያንቀሳቅሰው በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተቀመጠው መሠረት ከመንግስት ከሚሰጥ ድጋፍ፣ ከስፖርት ማዘውተሪያና ከመዝናኛ ገቢ፣ ከንብረት ሽያጭና ኪራይ፣ ከስጦ ና ዕርዳ ፣ ከማስ ወቂያና ስፖንሰርሺፕ፣ ከዓመ ዊ አባልነት ክፍያ፤ ከአትሌት ወኪሎች ና ከሌሎች ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች በሚሰበስበው ገቢ ነው፡፡

10. በዚህም መሠረት በ1998፣ 1999 እና 2000 በጀት ዓመታት በቅደም ተከተሉ መሠረት ብር 12.5 ሚሊዮን፣ ብር 11.6 ሚሊዮን እና ብር 13.2 ሚሊዮን የሰበሰበ ሲሆን፣ በነዚሁ በጀት ዓመታት ብር 11.7 ሚሊዮን፣ ብር 16.4 ሚሊዮን እና ብር 22.7 ሚሊዮን ወጪ አድርጓል፡፡ ፡፡ በ1999 እና በ2000 በጀት ዓመታት በተከታታይ ብር 4.8 ሚሊዮን እና 9.5 ሚሊዮን ወጪው ከፌዴሬሽኑ ዓመታዊ ገቢ በልጦ ታይቷል፡፡ ይህ በብልጫ የታየ ወጪ የተሸፈነው ባንክ ከሚገኝ የፌዴሬሽኑ ተቀማጭ ሂሳብ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር በአገሪቱ ውስጥ የአትሌቲክስ ስፖርትን የማስፋፋት ሥራን፣ በዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድሮች እየታየ ያለው ውጤት ቀጣይነት ንዲኖረው የሚደረገውን ንቅስቃሴ ንዲሁም የፌዴሬሽኑ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት በብቃት እየተከናወነ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፣ አሠራሩ የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ ሆኖ ካልተገኘም ውጤ ማ ንዳይሆን ያደረጉትን ችግሮች በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለሥራ አመራሩ ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች፤

12. ከላይ የተገለጸው የኦዲት ዓላማ ለማሳካት ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተመረጡ ሲሆን፣ ነርሱም፡-

1. በሀገሪቱ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት አጥጋቢና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣
    - 1.1. የአትሌቲክስ ስፖርትን በሀገር አቀፍ ደረጃ በማስፋፋት ብቁ እና ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት የተዘረጋው አሠራር አጥጋቢና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣
    - 1.2. በሀገሪቱ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የተዘረጋው የሥልጠናና የውድድር ሥርዓት ግልጽ፤ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣
2. በፌዴሬሽኑ የአትሌቲክስ ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ፣ አጠባበቅ፣ አጠቃቀምና ልውውጥ አጥጋቢ እና አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ፣
3. የአትሌቲክስ ስፖርትን በብቃት ለማከናወን እንዲቻል በፌዴሬሽኑ የሚከናወኑ የአቅም ግንባታ እንቅስቃሴዎች አጥጋቢነትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፤

13. የፌዴሬሽኑን የመተዳደሪያ ደንብ፤ የተለያዩ መመሪያዎች፤ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤዎች እንዲሁም የዓለም አቀፉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የመረጃ መረብን መሠረት በማድረግ ለዝርዝር ኦዲቱ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የፌዴሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎች በተዘጋጁት የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ አስተያየት እንዲሰጡባቸው ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ፤

14. ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ1998 ስከ የ2001 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በፌዴሬሽኑ የተከናወኑ ተግባራትን ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሲሆን፣ ፌዴሬሽኑን የሚመለከቱ የተለያዩ መረጃዎችን በመመርመር፣ ማብራሪያ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ለሚመለከታቸው የፌዴሬሽኑ የሥራ ላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ብሔራዊ አትሌቶች እንዲሁም ሌሎች አትሌቶች ልምምድ በሚያደርጉበትና ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ላይ በአካል በመገኘት ማስረጃዎችን በመሰብሰብ ነው::

15. በተጨማሪም በፌዴሬሽኑ ድጋፍና ክትትል ከሚደረግላቸው እና በተለያዩ ክልሎች ከሚገኙ የታዳጊ ወጣቶች አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ፕሮጀክቶች መካከል ከተሰጣቸው ትኩረት እንዲሁም ሁሉንም ለማዳረስ ከሚወስደው ጊዜና ወጪ አንፃር በናሙና በመምረጥ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እና በኦሮሚያ ክልሎች በያንዳንዳቸው ሦስት፤ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር አንድ በድምሩ ሰባት የ ዳጊ ማሰልጠኛ ፕሮጀክቶችን እንዲሁም በቆጂ እና አገረ ሰላም የሚገኙትን ሁለት የወጣቶች ማሰልጠኛ ማዕከላት እና በናሙና የተመረጡ ሰባት ክለቦችን በአካል በመጎብኘትና ማብራሪያ ለሚያስፈልጋቸው ሁኔታዎች የሚመለከታቸውን የሥራ ኃላፊዎች በማነጋገር እና መጠይቅ ተልኮላቸው እንዲሞሉ በማድረግ ተጨማሪ መረጃ የማሰባሰብ ሥራ ተከናውኗል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

## I. በሀገሪቱ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት አጥጋቢና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣

### 1.1 የአትሌቲክስ ስፖርትን በሀገር አቀፍ ደረጃ በማስፋፋት ብቁ እና ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት የተዘረጋው አሠራር አጥጋቢና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

**የአትሌቲክስ ስፖርትን በኃላፊነት የሚያንቀሳቅሱ አካላት አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሠራርን በተመለከተ፤**

16. በሁሉም ክልሎች የአትሌቲክስ ስፖርትን በኃላፊነት የሚያንቀሳቅሱ አካላት(የክልል አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች) እንዲቋቋሙ እና እንዲደራጁ ሊደረግ ይገባል፡፡

17. አትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ብሎም ሀገሪቱን ወክለው በተለያዩ ዓለም አቀፍ እና አህጉር ደረጃ በሚዘጋጁ የአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ የሚወዳደሩ ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት በሁሉም ክልሎች ከታች ከቀበሌ እና ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ ተገቢው ትኩረት ተሠጥቶት ስፖርቱን ለማስፋፋት የሚያስችል አደረጃጀት አልተዋቀረም፡፡ በተመረጡ ክልሎች በአካል በመገኘት ለማየት እንደተቻለው በአትሌቲክስ ስፖርቱ ዙሪያ ኃላፊነት ያለባቸው የክልል፣ የዞንና የወረዳ አመራር አባላት በአብዛኛው በሥልጠና ጣቢያዎችም ሆነ በስልጠና እና በውድድር ላይ ለሚከሠቱ ችግሮች ተገቢውን ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት ድክመት ይታይባቸዋል፡፡ በተለይም ለታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች ሥልጠና፣ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉ የባለድርሻ አካላት አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ያልተቀመጠ ሲሆን፣ ስፖርቱ በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲዘወተር እና እንዲስፋፋ ለማድረግ የተቀናጀ እና ወጥ አሠራርን የተከተለ የአተገባበር ስልት አልተቀየሰም፡፡

18. ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ተጠይቀው በሰጡት መልስ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የፌዴሬሽኑ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ኃላፊነት ሆኖ ሳለ ይህን ጉዳይ አጠናክሮ በተቀናጀ

መልኩ ለማከናወን የሚያስችል ፖሊሲ ባለመቀረፁ የጎላ ሥራ አለመከናወኑን እና በዚህም ላይ በመንግስት በኩል ትኩረት ተሰጥቶት መሠራት እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

19. በኦዲቱ ወቅት እንደተገነዘብነው በክልል የሚመለከታቸው አካላትም ሆኑ አገር አቀፍ ፌዴሬሽኑ የክልል ፌዴሬሽኖች ተጠናክረው እና እራሳቸውን ችለው የሚንቀሳቀሱበትን መንገድ ለማመቻቸት ተቀናጅተው አለመሥራታቸው የአትሌቲክስ ስፖርቱ በተሻለ ሁኔታ እንዳይስፋፋ አስተዋጽኦ አድርጓል የሚል ዕምነት አለን፡፡

20. ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ የሚመለከታቸው አካላት ተባብረው እና ተቀናጅተው የሚሠሩበት ሁኔታ ካልተመቻቸ፣ ሥልጣንና ተግባራቸው በግልጽ ተቀምጦ ካልተደራጁ እና ስለስፖርት አስተዳደር ተገቢውን ግንዛቤ ካላገኙ ስፖርቱን በተሟላ እና በተሻለ ሁኔታ በማጠናከር በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ለማስፋፋት፣ ለማሣደግ እና ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት የሚደረገውን እንቅስቃሴ ከግብ ለማድረስ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

## <u>የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የሚያስፈልጉ ደንቦችና መመሪያዎችን በተመለከተ፤</u>

21. የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የሚያስፈልጉ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ወዘተ በጥናት ሊዘጋጁና በየጊዜው ወቅታዊነታቸው እየተጠበቀ በየደረጃው ለሚገኙ አግባብነት ላላቸው አካላት ሊሰራጩ ይገባል፡፡

22. በዓለም አቀፉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በአትሌቲክስ ዙሪያ በየጊዜው የሚወጡ እና የሚሻሻሉ መመሪያዎች እና ሌሎች መረጃዎች እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው እየተዘጋጁ ከፌዴራል ጀምሮ በየደረጃው ለሚገኙ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲሰራጩ አይደረግም፡፡ በተወሰነ ደረጃ በፌዴሬሽኑ በራሱም ሆነ በዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን (IAAF–International Amateur Athletics Federetion) በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ የተዘጋጁ የተለያዩ መረጃዎች (መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ የሥልጠና ሰነዶች ወዘተ.) ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው የተለያዩ ሥልጠናዎች እና አውደ ጥናቶች ለሚካፈሉ ተሳታፊዎች ቢሠጡም መረጃዎቹን የወሠዱ ተሳታፊዎቸ እንደግል ንብረታቸው በመቁጠር ወክሎ ለላካቸው አካል የማያደርሱበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በእኛ እምነት ይህ ሊሆን የቻለው ከአገር አቀፍ

ፌዴሬሽኑ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ ያሉ አስፈጻሚ አካላት ያላቸው የቅንጅታዊ አሠራር፣ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ደካማ በመሆኑ ነው።

23. በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ ተግባራዊ የሆኑ ዓለም አቀፍ መመሪያዎችን፣ ደንቦችን፣ በየጊዜው የሚታዩ ለውጦችን እና መሻሻሎችን እንዲሁም በፌዴሬሽኑም ሆነ በአይ.ኤ.ኤ.ኤፍ (IAAF ) የሚዘጋጁ መረጃዎች አቅም በፈቀደ መጠን ወቅቱን ጠብቀው ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ታችኛው የአትሌቲክስ ስፖርቱ የሚመለከታቸው አካላት ድረስ የሚሠራጩበት ሁኔታ አለመመቻቸቱ በየደረጃው የሚገኙ ባለሙያዎች የአትሌቲክስ ስፖርቱን በተመለከተ ወቅታዊ እና የተሻለ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው በማድረግ የአትሌቲክስ ስፖርቱ እንቅስቃሴ ወቅቱ በሚጠብቀው ደረጃ እንዳይሻሻል ተጽዕኖ ያሳድራል።

## <u>የፋይናንስ ድጋፍ ማሰባሰብን በተመለከተ፤</u>

24. ፌዴሬሽኑ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት ተገቢ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልት ነድፎ ሊንቀሳቀስ ይገባዋል።

25. በ1999 በጀት ዓመት በዓለም አቀፍ ውድድሮች በቡድን ከሚገኝ ውጤት ብር 300,000.00 (ሶስት መቶ ሺህ ብር) ይገኛል ተብሎ በዕቅድ ቢያዝም ብር 36,065.27 ብቻ መሰብሰቡን ለማወቅ ተችሏል። ስለሁኔታው የአስተዳደር እና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዋ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ገቢው ይገኝባቸዋል የተባሉት ውድድሮች የሚከናወኑት እንደ አውሮፓ የዘመን አቆጣጠር ሲሆን፣ የፌዴሬሽኑ ዕቅድ ግን በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በመሆኑ የተፈጠረ ልዩነት እንደሆነ ገልጸዋል።

26. በበጀት ዓመቱ ይገኛል ተብሎ በዕቅድ የሚያዘው ገቢ የዘመን አቆጣጠር ልዩነቶችን ባገናዘበ ሁኔታ ሊያዝ ሲገባው ይህንን ባገናዘበ መልኩ ያለመያዙ ከአቅም በላይ የሆነ የሥራ ዕቅድ እንዲያዝና አፈፃፀሙም እንዲዛባ የሚያደርግ ይሆናል።

27. በአራት ክልሎች ለተቋቋሙት የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት የገንዘብ እና የማቴሪያል ድጋፍ የሚያደርገው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ብቻ መሆኑ ታውቋል። የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጋቸው የድጋፍ አይነት እና መጠን ከፍተኛና ከፌዴሬሽኑ ከአቅም በላይ በመሆኑ፣ ስፖርቱ ህዝባዊ መሠረት እንዲኖረው ህብረተሰቡ እና ባለሀብቶች ለአትሌቲክስ ስፖርት መስፋፋት ድጋፍ

እንዲያደርጉ የጎላ ጥረት መደረግ ይገባዋል፡፡ ሆኖም ፌዴሬሽኑ የተሻለ ድጋፍ እና ገቢ የሚገኝባቸውን ምንጮች በአግባቡ አለመጠቀሙ እና ኅብረተሰቡም ሆነ ባለሃብቶች ለአትሌቲክስ ስፖርቱ መስፋፋት ድጋፍ እንዲያደርጉ በቂ ጥረት አለመደረጉ አስተማማኝ አቅም በመፍጠር ስፖርቱን ለማስፋፋት አላስቻለም፡፡

28. ለሰንዳፋ አትሌቲክስ መንደር ግንባታ ገንዘብ ለመለገስ ቀደም ሲል ቃል የተገባ ቢሆንም ገንዘቡ እንዲሰበሰብ ጥረት አልተደረገም፡፡ የተጀመረው የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብርም ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት ተጠናክሮ እንዲቀጥል አልተደረገም፡፡ ለአትሌቲክስ መንደሩ ግንባታ ገቢ ማስገኛ ዶክመንተሪ ፊልም ቢዘጋጅም ለዕይታ ቀርቦ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የሚደረግበት ሁኔታ አልተመቻቸም፡፡

29. ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ አስተዳደር እና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬቷ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በወቅቱ በነበሩ የገቢ አሰባሳቢ የኮሚቴ አባላት መካከል አለመስማማት በመከሰቱ ለአትሌቲክስ መንደሩ ግንባታ ገቢ ለማስገኘት የሚያስችሉ ዕድሎችን ለመጠቀም የተሻለ እንቅስቃሴ አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ተጠይቀው በሰጡት መልስ በአጠቃላይ በሠንዳፋ አትሌቲክስ መንደር ግንባታ ዙሪያ ፌዴሬሽኑ ምንም ዓይነት መረጃ እንደሌለው፤ ሆኖም በሀገር አቀፍ ደረጃ በፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የሚመራ የስፖርት ፈንድ አሰባሳቢ ኮሚቴ በመዋቀሩ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑም የዚህ ኮሚቴ አባል በመሆን የገቢ ማሰባሰብ ሥራ በመከናወን ላይ እንደሚገኝ፤ ከዚህም ስፖርትን ለማስፋፋት በጥቅል ከተሰበሰበው ጠቅላላ ገንዘብ ውስጥ ለአትሌቲክስ ስፖርት ማስፋፊያም የተወሰነ ይደርሰዋል የሚል ግምት ስላላቸው በዚያ የተለያዩ የአትሌቲክስ ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን የማስፋፋት ሥራ ለማከናወን እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

30. የሰንዳፋ የአትሌቲክስ መንደር በታቀደለት ጊዜ ውስጥ አለመጠናቀቁ ለአትሌቲክሱ እድገት ሊኖረው የሚችለውን አስተዋጽዖ እንዳያበረክት አድርጓል፡፡ ይህም ሁኔታ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለአትሌቲክስ መንደሩ ግንባታ ሥራ ተገቢውን ትኩረት እንዳልሰጡት ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ለአትሌቲክስ መንደሩ ማስገንቢያ ገቢ ማስገኛ የተዘጋጀው ዶክመንተሪ ፊልም ለዕይታ ቀርቦ ገቢ እንዲያስገኝ ያለመደረጉ ለዝግጅቱ የወጣው ገንዘብ ካለምንም ጥቅም እንዲቀር እና ለግንባታ ማከናወኛ የተሻለ ገንዘብ እንዳይገኝ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## ዝቅተኛ ተሳትፎ እና ውጤት የሚታይባቸው የአትሌቲክስ ስፖርት ውድድር መስኮችን በተመለከተ

31. በአትሌቲክስ ስፖርት ዝቅተኛ ተሳትፎ እና ውጤት የሚታይባቸውን የውድድር መስኮች ለማሻሻል ትኩረት ሊሠጠው ይገባል፡፡

32. በአጭር ርቀት፣ በሌሎቹም ዝቅተኛ ተሳትፎ በሚደረግባቸው እና ምንም ተሳትፎ በሌለባቸው የአትሌቲክስ ዘርፎች ላይ ትኩረት ተሠጥቶ እየተሠራ ካለመሆኑም በላይ ለነዚህ የአትሌቲክስ ዘርፎች በፌዴሬሽኑ ደረጃ የተሻሉ መሣሪያዎች ያሉ ቢሆንም በክልል እና በክለቦች ተገቢው የሥልጠና ቁሳቁሶች መሣሪያዎች አልተሟሉም፡፡

33. የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት እና የፌዴሬሽኑ ቴክኒክ ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ ዝቅተኛ ተሣትፎ ባለባቸው የአትሌቲክስ ዘርፎች /አጭር ርቀት፣ ዝላይ…/ በፌዴሬሽኑ ደረጃ በቂ የሥልጠና መሣሪያዎች ቢኖርም ወደ ክልል እና ወረዳዎች በሚዘልቅበት ጊዜ ለእነዚህ ውድድሮች የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ተሟልተው አለመገኘታቸውን፣ በተጨማሪም በተጠቀሱት የውድድር ዘርፎች በቂ ባለሙያ ያለመኖሩ በዘርፉ ውጤታማ ሥራ ለመስራት አለማስቻሉን፤ ሆኖም እነዚህን ሁኔታዎች ለመለወጥ ፌዴሬሽኑ እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

34. ፌዴሬሽኑ ዝቅተኛ ተሳትፎ እና ውጤት በሚታይባቸው የአትሌቲክስ ስፖርቶች ላይ ትኩረት ሠጥቶ አለመሥራቱ እና ለነዚህ የአትሌቲክስ ስፖርቶች የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች በክልል፣ በወረዳና በክለቦች ደረጃ እንዲሟላ ያለመደረጉ በነዚህ ዘርፎች ተሰጥኦ ያላቸው አትሌቶች ያላቸውን ችሎታ አሻሽለው የተሻለ ውጤት ለማምጣት እንዳይችሉና አገሪቱ በዚህ ዘርፍ ውጤት እንዳታስመዘግብ የሚገደብ ይሆናል፡፡

## 1.2. በሀገሪቱ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የተዘረጋው የሥልጠናና የውድድር ሥርዓት ግልጽ፤ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣

### በብሔራዊ አትሌትነት የሚታቀፉ አትሌቶች ምርጫ በተመለከተ፣

35. ሀገርን ወክለው በተለያዩ አህጉር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የሚወዳደሩ አትሌቶችን ለማፍራት በብሔራዊ አትሌትነት የሚታቀፉ አትሌቶችን መምረጫ ግልጽ የሆነ መስፈርት ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡

36. በብሔራዊ አትሌትነት የሚታቀፉ አትሌቶች መምረጫ መስፈርት በየዓመቱ እንደ አዲስ እየተዘጋጀ ምርጫ የሚከናወን መሆኑን እና በአለፉት ሶስት ተከታታይ ዓመታት ማለትም በ1999፣ 2000 እና በ2001 ዓመታት የብሔራዊ አትሌቶች በዚህ መልክ እንዲመረጡ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለ2001 ዓ.ም ሀገርን ወክለው በተለያዩ ዓለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃ በሚዘጋጁ ውድድሮች ላይ የሚወዳደሩ አትሌቶችን ለማፍራት በብሔራዊ አትሌትነት ለመምረጥ ፌዴሬሽኑ እንደ ዋና የመምረጫ መስፈርት የተጠቀመበት አትሌቶቹ በርቀቱ ያስመዘገቡት የተሻለ ሰዓት (Minima) ቢሆንም የተመረጡት አትሌቶች ያስመዘገቡት የተሻለ ሰዓት ተሟልቶ አልተገለፀም፡፡ የተመረጡትን አትሌቶች የሚያሳየው መረጃም በሚመለከተው የፌዴሬሽኑ አካል መጽደቁን እና ትክክለኛነቱን የሚያሳይ ማረጋገጫ አልተገኘም፡፡

37. ለብሔራዊ አትሌትነት የተመረጡት አትሌቶች በፌዴሬሽኑ የተዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት ተጠብቆ የተመረጡ መሆኑ በሚመለከተው የፌዴሬሽኑ አካል የተረጋገጠበት መረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ ምርጫው ግልጽነትን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ አላስቻለም፡፡ ይህም ሁኔታ ለተለያዩ የአሠራር ድክመቶች መንገድ የሚከፍት ይሆናል፡፡

38. በ2001 ዓ.ም በብሔራዊ አትሌትነት በማቀፍ ለማሠልጠን የታሰበው ጠቅላላ የአትሌቶች ብዛት 110 ብቻ ሲሆን በዚህ ዓመተ ምህረት በአጠቃላይ የተያዙት አትሌቶች ብዛት ግን በእጥፍ በመብለጥ 202 መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ቁጥራቸው በእጥፍ ሊጨምር የቻለበትን ሁኔታ የሚያስረዳ መረጃ ለማግኘት እና

ተጓዳኝ የሆኑ ጉዳዮች ማለትም በጀት እና ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች የተሟሉ ለመሆኑ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

## ሀገርን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶች ምርጫን በተመለከተ

39. በብሔራዊ አትሌትነት ከታቀፉት አትሌቶች መካከል ሀገሪቱን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶች ለመምረጥ የሚያገለግል ግልጽ የሆነ መስፈርት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

40. አትሌቶች ሀገራቸውን ወክለው ለሚያደርጓቸው ውድድሮች ተመራጭ ለመሆን በሚወዳደሩበት ርቀት (event) ያላቸው የሠዓት (minima) መጠን እንደ ዋንኛ መመዘኛ የሚወሰድ ሲሆን፣ በብሔራዊ አትሌትነት የሚታቀፉ አትሌቶችን ለመምረጥ በተቀመጠው የመምረጫ መስፈርት ላይ እንደታየው በተመሳሳይ አትሌቶቹ ያስመዘገቡት ያላቸው የሠዓት (minima) ውጤት ከ4 ወር በፊት መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ ሆኖም ይህ ውጤት ከመቼ እስከ መቼ የተመዘገበ መሆን እንደሚገባው በግልጽ የጊዜ ገደብ አልተቀመጠለትም፡፡ በተጨማሪም አትሌቶች ለውድድር ብቁ መሆን አለመሆናቸው የሚወሰነው በአንድ ሐኪም አስተያየት ብቻ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሀገሪቱን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶች ለመምረጥ የተዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት በፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባዔም ሆነ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ለመጽደቁ የሚረጋገጥበት ምንም አይነት ፊርማም ሆነ ማህተም የሌለው በመሆኑ ይህ የመምረጫ መስፈርት በፌዴሬሽኑ እውቅና ተዘጋጅቶ ተቀባይነት አግኝቶ ተግባራዊ እንዲሆን የቀረበ ለመሆኑ ለማረጋገጥ አያስችልም፤

41. ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት፣ የጽ/ቤት ኃላፊ እና የቴክኒክ ዲይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ በአንድ ሐኪም ብቻ የሚሰጠው አስተያየት ቀርቶ ይህን ተግባር የሚያከናውን የሕክምና ቡድን መቋቋም እንዳለበት የታመነበት መሆኑን፤ ሆኖም በአትሌቶች በኩል ለሚቀርቡ ቅሬታዎች በወቅቱ አግባብነት ያላቸው እርምጃዎች የተወሰዱ እና ለመወሰዳቸውም መረጃዎች ያሉ መሆኑን እና በብሔራዊ አትሌትነት የሚታቀፉ አትሌቶች ምርጫም ሆነ ተመርጠው ሲሰለጥኑ ከቆዩት የብሔራዊ አትሌቶች መካከል ሀገርን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶችን በመምረጥ ዙሪያ የተጠቀሱት ችግሮች መነሻ የፌዴሬሽኑ መረጃ አያያዝ ላይ

የሚታየው ክፍተት መሆኑን በመጥቀስ ለወደፊት የፌዴሬሽኑን የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ለማስተካከል ጥረት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

42. ሀገርን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶች መምረጫ መስፈርት ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተሟልቶ አለመዘጋጀት እና የአትሌቶችን የጤንነት ብቃት በአንድ የጤና ባለሙያ ብቻ መረጋገጡ የተለያየ አተረጓጎም የሚያስከትል፣ ሚዛናዊ የሆነ አስተያየት ለመስጠት የማያስችል እና ሀገሪቱን ወክለው ብዙ አስተዋጽኦ ያደረጉ እና ሊያደርጉ የሚችሉ አትሌቶች ላይ ቅሬታ ሊያስከትል የሚችል ይሆናል፡፡

## ብሔራዊ ቡድኑን የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞች ምርጫን በተመለከተ

43. በየውድድር ዘርፉ የብሔራዊ ቡድን አትሌቶችን እና አገርን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶችን የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መስፈርት ሊኖር እና በመስፈርቱ መሠረት ምርጫው ሊከናወን ይገባል፡፡

44. በየውድድር ዘርፉ የብሔራዊ ቡድን አትሌቶችን እና አገርን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶችን የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞችን ለመመደብ ፌዴሬሽኑ ያዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት ውስጥ ዋነኛው መስፈርት የአሠልጣኞች የትምህርት ደረጃ ሲሆን፣ በዋና አሰልጣኝነት የሚመደብ አሠልጣኝ ቢያንስ ቢ.ኤ ዲግሪ ሊኖረው እንደሚገባ ተቀምጧል፡፡ ሆኖም ለ3000 ሜትር መሰናክል እና ለእርምጃ ከተመደቡት አሠልጣኞች መካከል የትምርት ደረጃቸው 12ኛ ክፍል እና 12 +3 የሆኑ እና መስፈርቱን የማያሟሉ አሰልጣኞች የተመረጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ፌዴሬሽኑ የምክትል ዋና አሠልጣኝ እና የረዳት አሠልጣኝነት የሥራ መደቦች የሌለው ሲሆን በነዚህ የሥራ መደቦች ላይ ግን አሠልጣኞች ተመድበው ተገኝቷል፡፡ ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት እና ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በብሔራዊ አሠልጣኝነት ለመመደብ እና በመስፈርቱ መሠረት ለመቅጠር ቢፈለግም መሥፈርቱን የሚያሟላ አሠልጣኝ ለማግኘት ባለመቻሉ መስፈርቱን ዝቅ በማድረግ ለመቅጠር መገደዳቸውን ገልጸዋል፡፡

45. ፌዴሬሽኑ በሌለው የሥራ መደብ አሰልጣኞቹን መመደቡ እና በፌዴሬሽኑ የተዘጋጀውን የመምረጫ መስፈርት የማያሟሉ አሰልጣኞችን መምረጡ ብቁ የሆኑ አሠልኞችን በመመደብ ዙሪያ የጎላ ክፍተት ከመፍጠሩም በላይ ለብልሹ አሠራር መንገድ የሚከፍት ይሆናል፡፡

## የአሠልጣኝነት እና የዳኝነት ኮርሶች ሥልጠና የሚሰጡ አሰልጣኞች እና ሰልጣኞችን በተመለከተ፤

46. የአሠልጣኝነትና የዳኝነት ኮርስ ሥልጠና የሚሰጡ አሠልጣኞች ለመምረጥ እና የኮርሱ ተሳታፊ የሚሆኑ ሰልጣኞችን ለመምረጥ የሚያገለግል ግልጽ የሆነ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡

47. የአሠልጣኝነትና የዳኝነት ስልጠና ኮርስ የሚሰጡ አሰልጣኞች ለመምረጥ የሚያገለግል ግልጽ የሆነ መስፈርት አልተዘጋጀም፡፡ የአሰልጣኝነት ኮርስ ተሳታፊ የሚሆኑ ሰልጣኞችን ለመምረጥ የሚያስችል መስፈርት ቢዘጋጅም በሚመለከተው የፌዴሬሽኑ አካል እንዲጸድቅ አልተደረገም፡፡ ሠልጣኞች በመስፈርቱ መሠረት የሚመረጡ መሆናቸውን ክትትል የማይደረግ መሆኑ እና ሥልጠና ለመስጠት በተሄደበት ክልል አራት ሠልጣኞች ብቻ በመገኘታቸው ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች አዳዲስ ሰዎች እንዲሰባሰቡ በማድረግ ሥልጠና እንዲሰጥ የተደረገበት ሁኔታ የተከሰተበት እና ለሚሰጠው ሥልጠና በትምህርት ደረጃም ሆነ በሙያ የማይመጥኑ ሠልጣኞች ተሳታፊ የሚሆኑበት ሁኔታ በተደጋጋሚ እንደሚያጋጥም ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

48. ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ የቴክኒክ ዳይሬክተር እና የልማትና ፕሮጀክት ኤክስፐርት ተጠይቀው በሰጡት መልስ በአገራችን በIAAF የወጣውን መስፈርት የሚያሟላ የአትሌቲክስ አሠልጣኝ ማግኘት ስለሚያስቸግር በቀጥታ ያንን መስፈት መጠቀም እንዳልተቻለ እና የሀገሪቱን ሁኔታ ያገናዘበ የአሠልጣኞች መምረጫ መስፈር ያልተዘጋጀው ለውድድር ተግባር ቅድሚያ ትኩረት በመሰጠቱ መሆኑን በመጥቀስ በ1993 ወደ 15 የሚሆኑ ባለሙያዎች ተለይተው የኢንስትራክተርነት ኮርስ እንዲወስዱ በማድረግ የአሠልጣኝነትና የዳኝነት አሠልጣኝ መሆን ይችላሉ ተብሎ ተለይተው እንደነበር፤ ሆኖም የአትሌቲክስ አሠልጣኝነት ኮርስ የሚሠጡ አሠልጣኞች በአካል ማጐልመሻ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ ያላቸው፣ የአይ.ኤ.ኤፍ እና የሀንጋሪ ኮርስ የወሠዱ እና ጥሩ የማስተማር ልምድ ያላቸው አሰልጣኝ በማለት እንደሚመረጡ ገልጸዋል፡፡ የሰልጣኞች ምርጫን በተመለከተ የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ተጠይቀው በሰጡት መልስ የፌዴሬሽኑ ተግባር ሥልጠና የሚሰጡ ባለሙያዎችን መላክ መሆኑ፣ በሠልጣኝነት የሚሳተፉ ተሳታፊዎችን የመምረጥ ተግባር የክልሎች እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

49. ፌዴሬሽኑ የሚያዘጋጀው ሥልጠና ውጤታማ ሊሆን የሚችለው በሚፈለገው ደረጃ ለማሰልጠን የሚችሉ አሰልጣኞች እና የተሰጠውን ሥልጠና በቀላሉ ተቀብለው ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚችሉ ሠልጣኞች ሲመረጡ እና ተሳታፊ ሲሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የአሠልጣኝነትም ሆነ የዳኝነት ሥልጠና የሚሰጡ አሠልጣኞች እና የሚሠለጥኑ ሠልጣኞችን ለመምረጥ የሚያስችል መስፈርት በቅድሚያ ተዘጋጅቶ እና በሚመለከተው የፌዴሬሽኑ አካል ጸድቆ ካልተቀመጠ እና የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ አሰልጣኞች እና ሠልጣኞች ካልተመረጡ ውጤታማ የሆነ ሥልጠና ለመስጠትም ሆነ የተሰጠውን ሥልጠና በአግባቡ ተቀብሎ ተግባራዊ የሚያደርግ ባለሙያ ለማፍራት ስለማያስችል የአትሌቲክስን ስፖርት በብቃት እና በጥራት ለማስፋፋትና ለሀገሪቱ የተፈለገውን ውጤት ለማስገኘት እንዳይቻል አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

## በአሰልጣኝነትና የዳኝነት ኮርስ ስልጠና ላይ የሚካፈሉ ሠልጣኞች ብዛትን በተመለከተ፤

50. በአሰልጣኝነትና የዳኝነት ኮርስ ስልጠና ላይ በአንድ አሠልጣኝ በአንድ ጊዜ 25 ሠልጣኞች ብቻ መሠልጠን ሲኖርባቸው በአብዛኛው ጊዜ ቁጥራቸው ከተጠቀሰው መጠን በላይ ለሆኑ ሠልጣኞች በአንድ አሰልጣኝ ስልጣና የሚሰጥበት ሁኔታ እንደሚታይ ለማወቅ ተችሏል፡፡

51. በአንድ አሰልጣኝ የሚሰጥ ሥልጠናን እንዲከታተሉ በእስታንደርድ የተቀመጠውን ብዛት ጠብቆ ሥልጠናው እንዲከናወን አለመደረጉ ሠልጣኞች በተፈለገው መልኩ ሥልጠናውን እንዳይከታተሉ በማድረግ ሥልጠናው የታለመለትን ዓላማ እንዳያሳካ ያደርጋል፡፡

## ለሠልጣኞች የሚሰጥ ፈተና ዝግጅትና ግምገማን በተመለከተ፤

52. ለአሰልጣኝነትም ሆነ ለዳኝነት ሠልጣኞች የሚሰጥ ፈተናን የሚያዘጋጅና ፈተናውን የሚገመግም ገለልተኛ አካል /ባለሙያ/ ሊኖር ይገባል፡፡

53. የአሰልጣኝነትም ሆነ የዳኝነት ሠልጣኞች ፈተና ማዕከላዊነትንና ወጥነትን በጠበቀ ሁኔታ በገለልተኛ አካል የማይዘጋጅ ሲሆን፣ ሥልጠናውን ለመስጠት በተመደቡ አሠልጣኞች ስልጠናው በሚሰጥበት ቦታ እና ወቅት ተዘጋጅቶ እንዲፈተኑ እና

እንዲታረም ከተደረገ በኋላ አሰልጣኞች የሠልጣኞችን ውጤት ይዘው ወደ ፌዴሬሽኑ እንዲመለሱ ይደረጋል፡፡

54. በፌዴሬሽኑ ተዘጋጅተው የሚሰጡ ሥልጠናዎች ላይ የሚሰጥ ፈተና ማዕከላዊነትን በጠበቀ እና ገለልተኛ በሆነ አካል እንዲዘጋጅ እና እንዲታረም አለመደረጉ ፈተናውና ምዘናው ወጥ እና ሠልጣኞችን በእኩል ደረጃ ለመመዘን የማያስችል ከመሆኑም በላይ ሥልጠናውን ማጠናቀቃቸውን በማረጋገጥ የሚሰጠው ሠርቴፊኬትም አንድ ወጥ እና ሚዛናዊነትን የተከተለ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

## የአሰልጣኝነት እና የዳኝነት ስልጠና ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትን በተመለከተ

55. የአሠልጣኝነትም ሆነ የዳኝነት ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓተ ትምህርት (curriculum) ተቀርጾ ተግባራዊ ሊደረግና በየጊዜው እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያ ሊደረግበት ይገባል፡፡

56. በ1996 ዓ.ም የወጣ ለአትሌቲክስ ሥልጠና እንዲያገለግል የተዘጋጀ የሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት (curriculum) ቢኖርም ለሚመለከተው የፌዴሬሽኑ አካል ቀርቦ የፀደቀ መሆኑን እና በየጊዜው ማሻሻያ የተደረገበት ለመሆኑ ማረጋገጫ ለማግኘት አልተቻለም፡፡

57. የአትሌቲክስ ጽ/ቤት ኃላፊው ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ ስለዚህ የሥልጠና ሥርዓት የሚያውቁት ጉዳይ እንደሌለ እና በአሁኑ ወቅት ፌዴሬሽኑ እየተጠቀመ ያለው የዓለም አቀፉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን (IAAF) የሥልጠና ሥርዓት እንደሆነ እና የሥልጠና ሥርዓት (curriculum) ማጽደቅ ሙያዊ ሥራ በመሆኑ የፌዴሬሽኑ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሊያፀድቀው አይገባም በሚል ገልጸዋል፡፡

58. የአሠልጣኝነትም ሆነ የዳኝነት ሥልጠና ለመስጠት የሀገሪቱን ሁኔታ ያገናዘበ እና ወጥ የሆነ የሥልጠና ሥርዓት (curriculum) ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ አለመዋሉ በፌዴሬሽኑ ተዘጋጅተው የሚሰጡ ሥልጠናዎች ከሀገሪቱ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ ለሠልጣኞች ማስተላለፍ የሚገባቸውን ክህሎት የሚያስተላልፉ መሆናቸውን ለመከታተል እና ሥልጠናዎች ወጥ እና ተመጣጣኝ ይዘት

እንዲኖራቸው ለማድረግ አያስችልም፡፡ በመሆኑም የሥልጠና አሰሠጣጡ ብቃት እና ውጤታማነት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## የሥልጠና ማቴሪያል ዝግጅትን በተመለከተ

59. የአሠልጣኝነት እና የዳኝነት ስልጠና ለመስጠት የሚያገለገል የሥልጠና ማቴሪያል ተዘጋጅቶ በሥልጠና ወቅት ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡ የአሠልጣኝነትም ሆነ የዳኝነት ስልጠና ለሚወስዱ ሠልጣኞች የሚያገለግሉ የስልጠና ማቴሪያሎች የማይዘጋጁ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ የአሠልጣኝነት እና የዳኝነት ሥልጠና እንዲሰጡ የሚመደቡ ባለሙያዎች ከዓለም አቀፉ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን (IAAF) የወሠዱትን የሥልጠና መረጃዎች እና ማንዋሎች በራሣቸው በመተርጐምና ይጠቅማሉ ብለው ያመኑባቸውን የተለያዩ ስፖርታዊ ፊልሞች በስልጠና ወቅት በማሣየት ስልጠና የሚሠጡ መሆኑን እና የተግባር ልምምዶችን በማስተማር ጥረት እንደሚያደርጉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. የስልጠና ማቴሪያል አንድ ወጥ በሆነ መልኩ ከአለም አቀፍ የስልጠና መረጃዎች እና ማንዋሎች ተገናዝበው አለመዘጋጀት ለሠልጣኞቹ በሥልጠናው ሊተላለፉ የሚገቡ ነጥቦችን በትክክል ለማስተላለፍ የማያስችል ከመሆኑም በላይ ሥልጠና አሰጣጡ የሀገሪቱን ሁኔታ ያገናዘበ እና አንድ ወጥ የሆነ ይዘት እንዳይኖረው እንዲሁም በሥልጠናዎቹ አማካኝነት ሊተላለፍ የሚገባው ክህሎት በብቃት እንዳይተላለፍ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

## የሥልጠና መርሐ ግብር ዝግጅትን በተመለከተ

61. ፌዴሬሽኑ በአትሌቲክስ ስፖርት የአሠልጣኝነት ስልጠና መርሃ ግብር ከማውጣቱ በፊት የክልሎችንና የክለቦች ፍላጐት ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ በፌዴሬሽኑ የሥልጠና መረሃ ግብር ሲዘጋጅ ክልሎች እና ክለቦች የተዘጋጀውን የሥልጠና መረሐ ግብር እንዲያውቁት ከማድረግ ውጭ የሥልጠና ፍላጐታቸው በቅድሚያ ታውቆ የሚካተትበት የአሠራር ሥርዓት አልተመቻቸም ፡፡

62. የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ በቅድሚያ የክልሎችን እና የክለቦችን የሥልጠና ፍላጐት ሳያካትት የሥልጠና መረሐ ግብር ካወጣ በኋላ እንዲያውቁት ብቻ መላኩ የእነዚህ አካላት የስልጠና ፍላጐትን ያገናዘበ ሥልጠና ለማዘጋጀት የማያስችል ከመሆኑም በላይ ክልሎች እና ክለቦች ሥልጠና መኖሩን በቅድሚያ እንዲያውቁት

ስለማያደርግ ለሥልጠናው ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ አያስችላቸውም፡፡ ይህ መሆኑ የሚሰጠው ሥልጠና ስኬታማነት ላይ የጎላ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

## በፌዴሬሽኑ ስር አትሌቶችን የሚያሠለጥኑ አሠልጣኞች ግምገማን በተመለከተ

63. በፌዴሬሽኑ በየደረጃው ተተኪ ንም ሆነ ነባር አትሌቶችን የሚያሠለጥኑ አሠልጣኞች የሚገመገሙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡

64. በኦዲቱ ወቅት ከተገኙ መረጃዎቸ ለመረዳት እንደተቻለው ፌዴሬሽኑ ብሔራዊ ቡድኑን የሚያሠለጥኑ አሠልጣኞችን የሥራ ክንውን በተመለከተ በየጊዜው ግምገማ የማያከናውን መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህንንም በተመለከተ የፌዴሬሽኑ የቴክኒክ ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ስልጠናው በምን አይነት ሁኔታ እየተከናወነ እንዳለ እና ምን ምን ችግሮች እንደተከሠቱ በየ15 ቀኑ አጠቃላይ ግምገማ እንደሚያከናውኑ ሆኖም እያንዳንዱን አሠልጣኝ ሥልጠናውን በሚያከናውንበት ወቅት ስላከናወነው ጠንካራም ሆነ ደካማ ተግባር ግምገማ የማይከናወን እና መረጃም እንዳልተያዘ፤ በአጠቃላይ የእያንዳንዱን አሠልጣኝ የአሠለጣጠን ሁኔታና ሂደት የተገመገመበት ሁኔታ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

65. ሀገሪቱን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶችን የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞች በተናጠል የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ በአግባቡ ማከናወናቸውን በተመለከተ ግምገማ አለማድረጉ በሥልጠና አሰጣጡ ላይ በአሠልጣኙ ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮችን በወቅቱ በማረም መፍትሄ እንዳያገኙ ከማድረጉም በላይ ብቃት ያላቸው አሠልጣኞችን በመለየት አትሌቶቹ የተሻለ ሥልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ አያስችልም፡፡

## የአትሌቲክስ ስፖርት አሠልጣኝነት የሙያ ፈቃድ ደረጃን በተመለከተ

66. በአትሌቲክስ ስፖርት በአሠልጣኝነት የሚሰማሩ ባለሙያዎችን ለመመደብ ፌዴሬሽኑ የሙያ ደረጃ ሊያወጣና የአሰልጣኝነት ፈቃድ በሚመጥኑት ደረጃ ሊሠጥ ይገባል፡፡

67. ፌዴሬሽኑ ለአትሌቲክስ ስፖርት አሠልጣኞች የሙያ ደረጃ አውጥቶ በየደረጃው ፈቃድ ለመስጠት በ1999 በጀት ዓመት ዕቅድ ቢይዝም በዕቅዱ መሠረት ተግበራዊ አላደረገም፡፡ ይህ ሥራ በቀጣይ ዓመታትም በዕቅድ ተይዞ ተግባራዊ አልሆነም፡፡

ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ የቴክኒክ ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ በአሁኑ ወቅት ፌዴሬሽኑ ያሰልጣኞችን የሙያ ደረጃ በማዘጋጀት ላይ እንደሆነ እና ክልሎች በቀረበው ረቂቅ ላይ ተወያይተው የሚሰጡትን አስተያየት በማካተት በቅርብ እንደሚጸድቅ ገልጸዋል ፡፡

68. የአትሌቲክስ አሠልጣኞች የሙያ ብቃት ደረጃ ወጥቶ ተግባራዊ አለመደረጉ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ አትሌቶች ደረጃቸውን በጠበቁ አሠልጣኞች ሰልጥነው ተፈላጊውን ውጤት ለማስገኘት የሚያስችል ተገቢ ስልጠና እንዳያገኙ የሚያደርግ በመሆኑ ብቃት ያላቸውን አትሌቶች ለማፍራት አያስችልም፡፡

## ውድድር ማካሄጃ መሳሪያዎችን በተመለከተ

69. ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው የአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ አስፈላጊውን የውድድር ማካሄጃ መሣሪያዎችን አሟልቶ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

70. የክዋኔ ኦዲቱ በተከናወነበት ወቅት በውድድር ቦታ በመገኘት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ፌዴሬሽኑ ባዘጋጃቸው የትራክ ውድድሮች ላይ የፎቶ ፊንሽ መሣሪያ እንደማይጠቀም ታይቷል፡፡ የፌዴሬሽኑ የቴክኒክ ኃላፊ ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ አንዳንድ ቴክኒካዊ እውቀት የሚጠይቁ እንደ ፎቶ ፊኒሽ ያሉ መሣሪያዎች ለመጠቀም የባለሙያ ችግር በማጋጠሙ የተበላሸበት እና የተፈላገውን ያህል አገልግሎት ላይ የማይውልበት ሁኔታ በመከሰቱ ከ16ኛው የአፍሪካ አትሌቲክሰ ሻምፒዮና በኂላ መጠቀም እንዳልተቻለ ገልጸዋል፡፡

71. የመሣሪያውን አጠቃቀም የሚያውቅ ባለሙያ ቢያንስ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ላይ አለመኖሩ እና እነዚህን መሳሪያዎች መጠቀም አለመቻሉ በተለይ በአጫጭር ርቀት ውድድሮች ላይ ብቃት ያላቸውን አትሌቶች በአግባቡ ለመለየት ስለማያስችል የዳኝነት ችግሮች እንዲከሰቱ እና አትሌቶችም ላይ ቅሬታ እንዲፈጠር ከማድረጉም በላይ በውድ ዋጋ የተገዙ መሳሪያዎችን ለብልሽት በማጋልጥ ለጥገና ከፍተኛ ወጪ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

## የታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክት አቀራረጽን በተመለከተ፤

72. ታዳጊ ወጣቶችን በአትሌቲክስ ስፖርት ለማሠልጠን የሚቀረጹ ኘሮጀክቶች በጥናት ላይ በመመርኮዝ ሊቀርጹና በየክልሉ ሊተገበሩ ይገባል፡፡

73. የታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክት ጣቢያ የሚቋቋሙባቸውን ክልሎች ለመለየት በጥናት የተዘጋጀ መስፈርት የለም፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የተቋቁሙት ፕሮጀክቶች በግልጽ በጥናት በተለየ መስፈርት ተለይተው አይደለም፡፡ ስለሁኔተው የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ተጠይቀው በሰጡት መልስ በጥናት የተዘጋጀ መስፈርት ባይኖርም አሁን በመተግበር ላይ ያሉት የታዳጊ ወጣቶች ማሠልጠኛ ኘሮጀክቶች የተመሠረቱት ቀደም ሲል ውጤታማ የሆኑ ቦታዎችን በመለየት መሆኑን እና ለወደፊት ለኘሮጀክቶች ምሥረታ የሚሆኑ መስፈርቶች በጥናት ሊዘጋጁ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

74. ይህ አሠራር ኘሮጀክት ጣቢያ ባልተቋቋሙባቸው ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ታዳጊ ወጣቶች በአትሌቲክስ ስፖርት ሥልጠና እድል የማግኘት ተስፋቸውን የሚያሣንስ ከመሆኑም በላይ በነዚህ ክልሎች ተተኪ አትሌቶችን ማግኘት የሚቻልበትን አጋጣሚ ለመጠቀም አያስችልም፡፡

## <u>በታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክቶች ላይ የሚደረግ ክትትልና ግምገማን በተመለከተ፤</u>

75. በየክልሉ የሚካሄዱ የታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክቶች ላይ በየዓመቱ ክትትልና ግምገማ ሊደረግ ይገባል፡፡

76. ፌዴሬሽኑ ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳ ስፖርት አመራር አካላት ጋር በመተጋገዝና በመቀናጀት በታዳጊ ወጣቶች የአትሌቲክስ ኘሮጀክቶች ላይ በፕሮጀክት ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሠረት በየጊዜው የክትትል እና የግምገማ ተግባር አከናውኖ አልተገኘም፡፡

77. ይህም ፌዴሬሽኑ እና በየደረጃው ኃላፊነት ያለባቸው የክልል አካላት በታዳጊ ወጣቶች የአትሌቲክስ ኘሮጀክት ጣቢያዎች ላይ ማድረግ የሚገባቸውን ክትትል በአግባቡ እንዲያከናውኑ ለማስተባበር የተደረገው እንቅስቃሴ እና ጥረት አጥጋቢ አለመሆኑን የሚያሣይ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ የታዳጊ ወጣቶች የአትሌቲክስ ስፖርት ማሠልጠኛ ጣቢያዎች ላይ ቀጣይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር አለመደረግ እንደ አቢይ የፕሮጀክቱ ዓላማ የተቀመጠውን ሀገርን ወክለው በአህጉርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊወዳደሩ የሚችሉ ብቃት ያላቸው ተተኪ አትሌቶች ለማፍራት የሚደረገውን ጥረት ውጤታማነት ይቀንሰዋል፡፡

78. ፌዴሬሽኑ በአንዳንድ የታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክት ጣቢያዎች ላይ ዓመታዊ ግምገማ ቢያደርግም የግምገማው ሪፖርት ግምገማው ለተከናወነባቸው የታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክት ጣቢያዎች እንደማይደርስ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የግምገማው ሪፖርት ለፕሮጀክት ጣቢያዎቹ እንዲደርስ አለመደረጉ የኘሮጀክት ጣቢያዎቹ ሊያሻሽሉ የሚገቡአቸውን ሁኔታዎች ተገንዝበው በወቅቱ እርምጃ እንዳይወስዱ እና ጠንካራ ሥራቸውን አውቀው አጠናክረው እንዳይቀጥሉ ያደርጋቸዋል፡፡

## ለታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች የሚደረግ ድጋፍን በተመለከተ፤

79. የታዳጊ ወጣቶች ማሠልጠኛ ጣቢያዎች የሚደረግላቸው የትጥቅም ሆነ የገንዘብ ድጋፍ በወቅቱ እንደማይደርስ እና የበጀት ዓመቱ ካለፈ በኋላ እንደሚያገኙ በናሙና በተመረጡ የታዳጊ ወጣቶች ማሠልጠኛ ጣቢያዎች በተደረገ የመስክ ጉብኝት ለመገንዘብ ተችሏል ፡፡

80. የትጥቅ እና ሌላ ዓይነት ድጋፍ የሚደረገው ታዳጊ ወጣቶቹ በሥልጠና ወቅት እንዲጠቀሙበት ታስቦ ሲሆን፣ በወቅቱ አለመድረሱ ሠልጣኞቹ ካለበቂ ትጥቅ እና ድጋፍ ሥልጠና እንዲሰጣቸው የሚያደርግ በመሆኑ ስልጠናው የተሳካ እንዳይሆን እና የታለመለትን ግብ እንዳይመታ ያደርገዋል፡፡

## በታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክት የሚታቀፉ ታዳጊ ወጣቶች አመራረጥን በተመለከተ፤

81. በታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክት የሚታቀፉትን ታዳጊ ወጣቶች ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ፌዴሬሽኑ በአትሌቲክስ ፕሮጀክቶቹ የሚታቀፉ ታዳጊ ወጣቶች የመመልመያ መስፈርት ቢያዘጋጅም ምልመላው በአግባቡ መመሪያውን ተከትሎ ስለመከናወኑ ከየፕሮጀክቶቹ ለፌዴሬሽኑ ከሚቀርብ ሪፖርት በስተቀር በአካል በመገኘት ክትትል አይደረግም፡፡

82. በናሙና በተመረጡ የታዳጊ ወጣቶች ማሠልጠኛ ጉብኝት ወቅት በፕሮጀክት የሚታቀፉት ታዳጊ ወጣቶች በየዓመቱ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የማይመለመሉ እና አንድ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ የሚመለመሉ በመሆኑ በምልመላው ወቅት ከ14 እስከ 17 ዓመት እድሜ ያላቸው ወጣቶች ተመጣጣኝ ባልሆነ የዕድሜ ደረጃ ያሉ ታዳጊዎች እንዲካተቱ በመደረጉ በልምምድም ሆነ በውድድር ወቅት ዕኩል ባልሆነ

የዕድሜ ደረጃ እንዲሰለጥኑ እና እንዲወዳደሩ የሚደረግ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአንዳንድ ፕሮጀክት ጣቢያዎች የታዳጊዎቹን ትክክለኛ ዕድሜን ለመለየት ችግር እንደሚያጋጥማቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

83. በአትሌቲክስ ፕሮጀክት ጣቢያዎቹ የታቀፉት ታዳጊ ወጣቶች በትክክል ለመምረጫ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የተመረጡ መሆኑን ፌዴሬሽኑ በአካል ተገኝቶ የቅርብ ክትትል አለማድረጉ በአመራረጥ ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ እና በቀጣይም ሊከሰቱ የሚችሉ የአፈጻጸም ችግሮችን ከወዲሁ ለማስወገድ አያስችልም፡፡ ምርጫው በጥንቃቄ በመስፈርቱ መሠረት ስለመከናወኑ የቅርብ ክትትል አለመደረጉ በስልጠና ወቅትም ሆነ በውድድር ጊዜ የዕድሜ አለመመጣጠን እንዲፈጠር በር የሚከፍት በመሆኑ በታዳጊ የአትሌቲክስ ሠልጣኞች እና ተወዳዳሪዎች ላይ ጭንቀት እና የሞራል ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡

## <u>በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት የታቀፉ ታዳጊ ሠልጣኞች ከፕሮጀክቱ የሚለቁበትን ጊዜ በተመለከተ፤</u>

84. በታዳጊ ወጣቶች አትሌቲክስ ፕሮጀክቶች የታቀፉ ታዳጊ ሠልጣኞች ዕድሜያቸው 17 ዓመት በላይ ሲሆን ከፕሮጀክት መልቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡

85. ምንም እንኳን አንድ የታዳጊ ፕሮጀክት ጣቢያ በውስጡ አቅፎ ሊይዛቸው የሚባው ዕድሜያቸው ከ17 ዓመት በታች የሆኑ ሠልጣኞችን ቢሆንም በአንዳንድ ፕሮጀክት ጣቢያዎች ታዳጊ ተብለው ከ17 ዓመት በላይ የሆኑ ወጣቶች ተካተው ተገኝተዋል፡፡

86. ይህም አግባብነት ያለው ዕድሜ ላይ የሚገኙ ተተኪ ታዳጊ ሠልጣኞች በፕሮጀክቱ ታቅፈው የስልጠናም ሆነ የስፖርት ትጥቅ ድጋፍ እያገኙ ሊሰለጥኑ የሚችሉበትን ዕድል በመዝጋት በፕሮጀክቱ ዓላማ መሳካት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

## <u>በታዳጊ አትሌቲክስ ፕሮጀክት የታቀፉ ሠልጣኞች የስልጠና ጊዜን በተመለከተ፤</u>

87. በታዳጊ ወጣቶች አትሌቲክስ ፕሮጀክት የታቀፉ ሠልጣኞች የስልጠና የጊዜ ሠሌዳና የቀለም ትምህርት የጊዜ ሠሌዳ ተጣጥሞ መቀናጀት አለበት፡፡

88. የሠልጣኞች የልምምድ ጊዜ በአንዳንድ ጣቢያዎች ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት እስከ 1፡30 ድረስ ሲሆን፣ ከተለያዩ ቦታዎች ሥልጠና ወደ ሚሰጥበት ቦታ መጥተው

ሥልጠናወን ከወሰዱ በኋላ ወደ ቤታቸው ተመልሰው ቁርስ በመብላት ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ጊዜው አጭር በመሆኑ ስለሚረፍድባቸው ያለምንም ቁርስ በቀጥታ ወደ ትምህርት ቤት የሚገቡበት ወይም የትምህርት ሰዓታቸው የሚረፍድባቸው ሠልጣኝ ተማሪዎች እንዳሉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

89. ከሥልጠና በኋላ ታዳጊ አትሌቶች ያለ ምንም ምግብ ወደ ትምህርት ቤት መሄዳቸው እና አርፍደው ወደ ትምርት ቤት መግባታቸው በአትሌቶቹ የቀለም ትምህርት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያለው ሲሆን፣ በጤንነታቸው ላይ ጉዳትና የመድከም ባህሪን ሊያስከትልባቸው ስለሚችል ስልጠናው የተሳካ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## <u>የታዳጊ ወጣቶች ስልጠና አሰጣጥ መመሪያን በተመለከተ፤</u>

90. የታዳጊ አትሌቲክስ ሥልጠና ለመስጠት ጾታን፣ ዕድሜንና ተሠጥኦን መሠረት ያደረገ የሥልጠና መመሪያ ሊዘጋጅ እና በዚህ መመሪያ መሠረት ሥልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

91. በክልል የታዳጊ ወጣቶች የአትሌቲክስ ኘሮጀክት ጣቢያዎች የሚሰጠውን የአትሌቲክስ ስፖርት ሥልጠናን ከዓለም አቀፍ የሥልጠና መርሆዎች ጋር አጣጥሞ ለማካሄድ የሚያስችል የታዳጊዎችን የጾታ፣ የዕድሜ እና የአካባቢ ሁኔታ ያገናዘበ የሥልጠና መመሪያ ተዘጋጅቶ አልተገኘም፡፡ በመስክ በተደረገ ጉብኝት በናሙና በታዩ የታዳጊ ወጣት አትሌቲክስ ማሠልጠኛ ጣቢያዎች በልምምድና ስልጠና ጊዜ ሴቶችና ወንዶች ታዳጊ አትሌቶች በጋራ ስልጠና እንደሚሰጣቸው እና እንደየጾታቸውና እድሜያቸው የተመጣጠነ ልምምድ እንደማይሠጣቸው ለመመልከት ተችሏል፡፡

92. ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለታዳጊ ወጣቶች የአትሌቲክስ ፕሮጀክት የሚሆን የሥልጠና መመሪያ በፌዴሬሽኑ ተዘጋጅቶ ለክልል ተወካዮች የተሠራጨ ቢሆንም አዲስ አበባም ሆነ ክልሎች ላይ ይህ መመሪያ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡ የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንትም ተጠይቀው በሰጡት መልስ የታዳጊ ወጣቶች ሥልጠናን ከዓለም አቀፍ ደንቦችና መርሆዎች ጋር አጣጥሞ የሚሄድ የመተዳደሪያ ሠነድ የተዘጋጀ ቢሆንም ደንቡ የህፃናት /ከ6-12 ዓመት/ አትሌቲክስ ሥልጠናን አለማካተቱን እና ለዚህም ምክንያቱ ከሀገሪቱ

ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ለመተግበር አስቸጋሪ በመሆኑ መሆኑን የገለጹ ቢሆንም የኦዲት ቡድኑ በሥልጠና ፕሮጀክቶች የመስክ ኦዲት ባከናወነበት ወቅት ለታዳጊ ወጣቶች የሚሰጥ የአትሌቲክስ ሥልጠናን በተመለከተ ዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ደንቦችና መርሆዎች እና የሀገሪቷን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጀ መመሪያ አላገኘም፡፡

93. ይህም ሁኔታ እድሜን፣ ፆታን እና አካባቢያዊ ሁኔታን በአገናዘበ መልኩ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የሚያግዙ መመሪያዎችን በማውጣት ስፖርቱን ከታች ጀምሮ ለማስፋፋት የሚደረገው ጥረት ውስን መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን፣ በተለያዩ ክልሎችና ከተሞች ላይ የተቋቋሙት የታዳጊ ወጣቶች የአትሌቲክስ ኘሮጀክቶች የታዳጊዎቹን ነባዊ ሁኔታ በአገናዘበ መልኩ ሥልጠና እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡ ፌዴሬሽኑ ያዘጋጀው መመሪያም ሆነ የመተዳደሪያ ደንብ እስከታች ድረስ አለመድረሱ በመረጃ አያያዝ እና በሥርጭት ላይ ችግር መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም የፕሮጀክት አሠልጣኞቹ ወጥነት ያለው ሥልጠና እንዳይሰጡ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ታዳጊ አትሌቶቹ ባላቸው የተፈጥሮ ልዩነት የተነሳ ያላቸውን ኃይልና ብቃት በተገቢው ጊዜና ወቅት እንዳይጠቀሙበት ያደርጋል፡፡

## <u>ለታዳጊ የአትሌቲክስ ሰልጣኞች መሰጠት ያለበትን የሕክምና አገልግሎት በተመለከተ፤</u>

94. ለታዳጊ የአትሌቲክስ ሠልጣኞች ከሥልጠናው ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥማቸው ጉዳት የህክምና አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል ፡፡ በአብዛኛዎቹ የታዳጊ ወጣቶች የሥልጠና ጣቢያዎች ታዳጊ ሠልጣኞች ከሥልጠና ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥማቸው ጉዳት የህክምና አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ አልተመቻቸም፡፡

95. ሠልጣኞች በስልጠና ወቅት የአካልም ሆነ የአዕምሮ ጤንነት ችግር ሲያጋጥማቸው በአፋጣኝ የጤና አገልግሎት አለማግኘታቸው ራሣቸውን በብቃት አዘጋጅተው በተለያዩ ውድድሮች ለመቅረብና ለመሣተፍ እንዳይችሉ በተከታታይ ከሥልጠና የመቅረት ብሎም እንዲያቋርጡ ያደርጋቸዋል፡፡

## በታዳጊ አትሌቶች ውድድር ላይ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ፤

96. ፌዴሬሽኑ የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት ውድድር በፕሮጀክት የታቀፉት ታዳጊዎች ብቻ የሚሳተፉበት እንዲሆን ተገቢውን ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

97. ለውድድር ውጤት ማማር ሲባል ብቻ ከዕድሜ በላይ የሆኑ እና በታዳጊ ፕሮጀክቱ ያልታቀፉ ወጣቶችን በማካተት በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጅ በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት ውድድሮች ላይ ክልሎች የሚቀርቡበት ሁኔታ በተደጋጋሚ እንደሚታይ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

98. ይህም የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት ዋና ዓላማ የሆነውን የዕድሜ ጉዳይ ትኩረት በመስጠት በዕድሜአቸው የሚያሳትፉ ክልሎች እና ወጣቶች ላይ ቅሬታ እና ተስፋ መቁረጥን በማስከተል የፕሮጀክቱ አብይ ዓላማ እንዳይሳካ አሉታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

## የአትሌት ማናጀሮች ፈቃድ አሠጣጥ እና ክትትልን በተመለከተ

99. በሀገሪቱ እየተንቀሳቀሱ ያሉት የአትሌት ማናጀሮች ፈቃድ ለመስጠትና ሁኔታውን ለመከታተል የሚያስችል ተገቢ ደንብ እና መመሪያ ሊዘጋጅ፤ የአትሌት ማነጀሮችም በተዘጋጀው ደንብና መመሪያ መሠረት ፈቃድ ሊያወጡ እና ፈቃዳቸውንም በየዓመቱ ሊያሳድሱ ይገባል፡፡

100. የአትሌት ማናጀሮችን በተመለከተ የተዘጋጀው ደንብ በፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለመጽደቁ የቀረበ ማረጋገጫ የለም፡፡ በዚህ ደንብ ላይ የአትሌት ማናጀሮች ከአትሌት፣ ከክለቦች እና ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር እንዴት ውል እንደሚያከናውኑ፤ ማናጀሮቹም ሆኑ ተጓዳኝ የሀገር ውስጥ ተዋዋዮች ያላቸው መብት እና ግዴታዎች እንዲሁም የፈቃድ አወጣጥ ሂደቱ ፣ የክፍያ መጠን እና የክፍያ ማሻሻያ እንዴት እንደሚከናወኑ በዝርዝር አልተገለጸም፡፡

101. የአትሌት ማናጀሮች ፈቃድ ለመስጠት የተዘጋጀው መመሪያ ያልተሟላ መሆን ማናጀሮቹ ግዴታቸውን በአግባቡ እየተወጡ መሆኑን እና የፌዴሬሽኑ፣ የክለቦች እና የአትሌቶች መብት በአግባቡ ስለመከበሩም ሆነ ተገቢውን ጥቅም እያገኙ መሆኑን ለመከታተል እዳይቻል ከማድረጉም በላይ ለብልሹ አሠራር መንገድ ይከፍታል፡፡

## በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ የሴቶች ተሳትፎን በተመለከተ፤

102. ፌዴሬሽኑ በአትሌቲክስ ስፖርት የሴቶች ተሳትፎ የሚጠናከርበትን እና የሚያድግበትን ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ በIAAF ህግ መሠረት ከሚመረጡ ኮሚቴዎች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ የሚገልጽ ቢሆንም በአትሌቲክሱ ዘርፍ በተለይ በአሠልጣኝነት እና በየደረጃው በሚገኙ የአመራር ቦታዎች ላይ የሴቶች ተሳትፎ እንዲጠናከር እና እንዲበረታታ ፌዴሬሽኑ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ለመጥቀስ ያህል ከብሔራዊ አትሌቲክስ አሠልጠኞች መካከል ሴት አሠልጣኞች ሶስት ማለትም አስራ አምስት በመቶ (15%) ብቻ ናቸው፡፡ የፌዴሬሽኑ የቴክኒክ ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው የዳኝነትም ሆነ የአሠልጣኝነት ስልጠና ሊሠጥ ሲታሰብ ክልሎች ቢያንስ ሃያ አምስት በመቶ (25%) ሴት ሠልጣኞች እንዲልኩ ፌዴሬሽኑ የሚያሳስብ ቢሆንም በክልሎች ድክመት ተግባራዊ ሳይሆን እንደሚቀር ገልጸዋል፡፡

103. በአሠልጣኝነትም ሆነ በየደረጃው በሚገኙ የአመራር ቦታዎች የሴቶች ተሳትፎ እንዲጠናከር ተገቢው ትኩረት እንዲሰጠው አለመደረጉ ሴቶች በዘርፉ ሊያበረክቱ የሚችሉትን አስተዋጽኦ በብቃት እንዲያከናውኑ የሚገድብ ከመሆኑም በላይ በዚህ ዙሪያ ሴቶች ለሚያቀርቡአቸው ጥያቄዎች ፍታዊ ምላሽ እንዳያገኙም ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

104. በአንዳንድ የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት አካባቢ የወላጆች ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ ታዳጊ ሴቶችን ወደ ሥልጠና የመላክ ፍላጎት ዝቅተኛ መሆኑን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም በአትሌቲክስ ስፖርት በቀጣይ የሴቶችን ተሳትፎ ለማስፋፋት እና ለማጠናከር ብሎም ሀገርን የሚወክሉ ተተኪ ሴት አትሌቶችን ለማፍራት የሚደረገው ጥረት ውጤት አናሳ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## የጸረ ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ ስምምነትን ተግባራዊ ማድርግን በተመለከተ

105. ፀረ ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ ኮንቬንሽንን (convention) ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው የአገር ውሰጥ ውድድሮች ላይ ተግባራዊ የሚያደርግበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ የፀረ ዶፒንግ ምርመራ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው የሀገር ውስጥ ውድድሮች በሚሳተፉ አትሌቶች ላይ አይደረግም፡፡ ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ

ሐኪም እና የቴክኒክ ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመመርመሪያ መሣሪያዎቹ ውድ በመሆናቸውና በባለሙያ እጥረት ምክንያት ተግባራዊ ማድረግ እንዳልተቻለ የገለጹ ሲሆን፣ የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንትም ስለሁኔታው ተጠይቀው የፀረ-ዶፒንግ ምርመራ ለማድረግና ቁጥጥር ለማከናወን ከፍተኛ በጀት እና ባለሙያ የሚጠይቅ በመሆኑ ተግባራዊ ለማድረግ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

106. ምርመራው በሀገር ውስጥ ውድድሮች አለመደረጉ በፌዴሬሽኑ የሚደረጉ ውድድሮች አለም አቀፍ ይዘት እንዳይኖራቸው ከማድረጉም በላይ ሀገሪቷ የምታፈራቸው አትሌቶች በአለም አቀፍ አትሌቲክስ ውድድሮች ተቀባይነት የሌላቸውን ሁኔታዎች ያልተላመዱ መሆናቸውን በወቅቱ ለመከታተል እና እርምጃ ለመውሰድ አያስችልም፡፡

## በውጭ ሀገራት በግል ውድድር ለማድረግ የሚጠይቁ አትሌቶች ፈቃድ አሠጣጥን በተመለከተ

107. አትሌቶች በውጭ አገር በግል ውድድር ለማድረግ ሲጠይቁ ፈቃድ የሚሰጥበት ግልጽ የሆነ መመሪያና መስፈርት ሊኖር ይገባል፡፡

108. በብሔራዊ አትሌትነት ያልታቀፈና ታዋቂ ያልሆነ አትሌት በግሉ ጥሪ ተደርጎለት የፈቃድ ጥያቄ ሲያቀርብ ፌዴሬሽኑ ስለማንነቱ መረጃ ከክለቡ እንዲያመጣ መጠየቅ ያለበት እና ብቃትና ችሎታ የሌለው መሆኑን ካመነበት ፌዴሬሽኑ በምትኩ ሌላ አትሌት መርጦ ለመላክ መደራደር የሚችል መሆኑን ይህንን በተመለከተ በተዘጋጀው መመሪያ ላይ ተቀምጧል፡፡

109. ይህ ሁኔታ በክለብ ሳይታቀፉ በግላቸው ውጤታማ የሆኑ እና ሊሆኑ የሚችሉ አትሌቶች ተሳትፎን የሚገድብ ሲሆን፣ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ወድድሮች ላይ በመሳተፍ ያስመዘገበው/ችው ሰዓት የተጠየቀውን ሚኒማ እስካሟላ ድረስ እና በሕጋዊ መንገድ ጥሪ በማግኘት ጥያቄውን ያቀረበውን/ችውን አትሌት ብቃትና ችሎታ የለህም/ሽም ብሎ ተጨባጭ በሆነ መንገድ ሊለካ በማይቻል ሁኔታ በምትክ ሌላ አትሌት ለመላክ መደራደሩ በአትሌቶቹ ላይ ቅሬታ ያስከትላል፡፡ ይህም ለብልሹ አሠራር መንገድ የሚከፍት ሲሆን፣ ህጋዊ በሆነ መንገድ ለፌዴሬሽኑ ጥያቄ ከማቅረብ ይልቅ በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ለመውጣት ጥረት ወደ ማድረግ እንዲገፋፋ ያደርጋል፡፡ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም

ከአገር በመውጣት በአሁኑ ወቅት ለሌሎች አገራት በመሮጥ ውጤታማ የሆኑ አትሌቶች መከሰት ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል፡፡

110. በግል የውጭ የአትሌቲክስ ውድድር ላይ ለመሳተፍ ጥያቄ ለሚያቀርቡ አትሌቶች በተዘጋጀው የፍቃድ መስጫ መስፈርት ሰነድ ላይ  አትሌቶቹ ፍቃድ ለመጠየቅ በሚመጡበት ጊዜ የት የት መሄድ እንዳለባቸው የሚጠቁም፣ የሥራ ሂደቱን (Flow chart) የሚያሣይ እና በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ተስተናግደው እንደሚጨርሱ የጊዜ ገደብን የሚገልጽ መግለጫ ያልተካተተ ሲሆን፣ የሥራ ሂደቱ (Flow chart) ለተጠቃሚዎች ሊታይ በሚችል ግልጽ በሆነ ቦታ ተዘጋጅቶ አልተቀመጠም፡፡  ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ተጠይቀው በሰጡት መልስ ወደ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ የተለያዩ ጉዳዮችን ለማስፈጸም የሚመጡ አትሌቶችም ሆኑ ሌሎች እንግዶች የሚስተናገዱበትን ሁኔታ የሚያመቻችና የሚያቀላጥፍ አሠራር በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ውስጥ ተካቶ እየታየ መሆኑን በመውጪያ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

111. ይህም አትሌቶቹ እንዴት እና በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መስተናገድ እንዳለባቸው ግንዛቤ እንዳይኖራቸው በማድረግ ግራ የመጋባት ሁኔታ የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ በአገልግሎት አሰጣጡም ላይ ተጠያቂነት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

112. በብሔራዊ የአትሌቲክስ ቡድን ውስጥ ተካተው በፌዴሬሽኑ የሚሰለጥኑ አትሌቶች በግል ለተለያዩ ውድድሮች ወደ ውጪ ሲሄዱ አሠልጥነው ለዚህ ያበቁአቸው ክለቦች እንዲያውቁ ሳይደረግ ፌዴሬሽኑ በራሱ ብቻ እንዲከናወን ያደርጋል፡፡ ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ተጠይቀው በሰጡት መልስ በክለቦች ዙሪያ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለማስተናገድ የክለቦች ማቋቋሚያ ረቂቅ ሠነድ መጽደቁን እና ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

113. ፌዴሬሽኑ ከየክለቦቹ ተመርጠው በብሔራዊ አትሌቲክስ ቡድን ውስጥ ለተመለከቱ አትሌቶቸ በተለያዩ አህጉርም ሆነ ዓለም አቀፍ ውድድሮች እንዲሳተፉ ፈቃድ ሲሰጥ አትሌቶቹን ያፈሩ ክለቦች የሚያሳውቅበት አሠራር አለመኖሩ እና ክለቦች በአፈሩአቸው አትሌቶች ላይ ያላቸው መብት በግልጽ ተቀምጦ አለመከበሩ በክለቦች ላይ ከፍተኛ የሆነ ቅሬታ እየፈጠረ ይገኛል፡፡

## ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌላቸው አትሌቶች በሀገር ውስጥ ልምምድ እንዲያደርጉ ፈቃድ መስጠትን በተመለከተ፤

114. በዜግነት ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ አትሌቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ልምምድ ማድረግ የሚችሉበት የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት በጥናት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

115. በዜግነት ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ አትሌቶች በአገር ውስጥ ልምምድ ለማድረግ የሚችሉበት ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በዜግነት ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ አትሌቶች መጥተው በትራክ ላይ ልምምድ የሚያደርጉ ከሆነ በፌዴሬሽናቸው በኩል ፍቃድ እንደሚጠይቁ፣ የመሮጫ ትራኩ ካለው ክፍተት አንፃር እየታየ ፍቃድ የሚያገኙ መሆኑን እና በተነጻጻሪ የሀገራችን አትሌቶች በሌላ ሀገር ሄደው እንዲለማመዱ ፈቃድ በመጠየቅ ልምምድ እንዲያደርጉ የሚደረግ መሆኑን፣ ይህ ተግባር በትብብር መልክ የሚከናወን እንጂ ምንም የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት እንደማያስፈልገው፤ ሆኖም ከትራክ ውጪ በሀገሪቷ ላይ የሚለማመዱ ከሆነ የፌዴሬሽኑ ሥልጣን ሣይሆን የሀገሪቱ መንግስት ሥልጣን እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

116. የሀገሪቱ መልክዐ ምድር ለአትሌቲክስ ውድድር ተፈላጊ ከመሆኑ አንፃር ብዙ የውጪ ሀገር አትሌቶች መጥተው ልምምድ ለማድረግ ፍላጎት ስላላቸው ብዙ ጥያቄ እንደሚያቀርቡ የሚታወቅ ቢሆንም ለሁኔታው ፌዴሬሽኑ ትኩረት እንዳልሰጠው እና ከትብብር ባለፈ መልኩ እንደ ገቢ ማግኛ ዘዴ ተመልክቶ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል እንዳላሳሰበ ያሳያል፡፡ የአትሌቲክስ ስፖርት ከስፖርትነቱ ባለፈ ለሀገሪቱ እንደ አንድ የገቢ ምንጭ ሊሆን ስለሚችል በዚህ መልክ ሊኖሩ የሚችሉ አጋጣሚዎችን ለመጠቀም ዝግጅት አለማድርጉ ሀገሪቱ ልታገኝ የምትችለውን ጥቅም እንዳታገኝ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

## ክሶች እና አቤቱታዎችን ገለልተኛ በሆነ አካል ማስተናገድን በተመለከተ፤

117. ከአትሌቲክስ ስፖርት ጋር የተያያዙ ክሶችንና አቤቱታዎችን የሚሠማ ከፌዴሬሽኑ መደበኛ ተግባራት ገለልተኛ የሆነ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊቋቋም ይገባል፡፡

118. አትሌቶች በተለያየ ጊዜ ቅሬታ የሚያቀርቡ ሲሆን፣ ለመጥቀስ ለ29ኛው የቤጂንግ ኦሎምፒክ በማራቶን እንዲሳተፉ ተመርጠው የነበሩት ሴት ተወዳዳሪዎች የተመደቡላቸው አሠልጣኞች እንዳልተመቹአቸው ቅሬታቸውን በመግለጽ በሥልጠና ላይ አልተሳተፉም፡፡ በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ በአትሌቶችም ሆነ በሌሎች አካላት የሚነሱ ቅሬታዎችንና የሚቀርቡ ክሶችን የሚሠማ ገለልተኛ አካል (ኮሚቴ) በፌዴሬሽኑ ባለመቋቋሙ ቅሬታቸው በገለልተኛ አካል አልታየላቸውም፡፡

119. ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ እና የቴክኒክ ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ክሶችና ቅሬታዎች ሲኖሩ መጀመሪያ ለቴክኒክ ክፍሉ የሚቀርቡ እና የሚታዩ መሆኑን፤ ቴክኒክ ክፍሉ በሠጠው ውሣኔ ያለመስማማት ካለ ለፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት እያለ በየደረጃው ለጠቅላላ ጉባዔ ከደረሠ በኋላ የጠቅላላ ጉባዔው የሚሠጠው ውሣኔ እንደሚጸና ገልጸዋል፡፡

120. ፌዴሬሽኑ የሚያስተናግዳቸው አትሌቶች ለሚያነሱአቸው ቅሬታዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የቴክኒክ ኮሚቴው ተጠያቂ የሚሆንበት አጋጣሚ የጎላ ስለሚሆን ችግሩን እራሱ እንዲፈታ ማድረጉ አግባብ ካለመሆኑም በላይ ገለልተኛ የቅሬታ ሰሚ አካል በሌለበት ሁኔታ በአትሌቲክሱ ዙሪያ በየጊዜው ለሚከሰቱ ችግሮች እና ቅሬታዎች ተቀባይነት ያለው ውሳኔ በዘላቂነት ለመስጠት አያስችልም፡፡

## <u>የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦች አደረጃጀትን የሚመለከት መመሪያ ማዘጋጀትን በተመለከተ</u>

121. ፌዴሬሽኑ የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦች እንዲደራጁ ለማድረግ የሚረዳ መመሪያ ማውጣትና ተፈፃሚነቱን መከታተል አለበት፡፡

122. የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦች እንዲደራጁ ለማድረግ የሚረዳ መመሪያ በረቂቅ መልክ የተዘጋጀ ቢሆንም ፀድቆ ሥራ ላይ አልዋለም፡፡ በብሔራዊ አትሌት የታቀፉት አትሌቶችን በተመለከተ ያፈሩዋቸው ክለቦች በአትሌቶቹ ላይ ሊኖራቸው የሚገቡ መብቶች በግልጽ አልተቀመጡም፡፡

123. ፌዴሬሽኑ ብሔራዊ የአትሌቲክስ ቡድን በሚል በቋሚነት በጀት እና አሠልጣኞች መድቦ ሥልጠና በመስጠት በዓለም ሻምፒዮና፣ በኦሎምፒክ፣ በአፍሪካ ጌምስና

አፍሪካ ሻምፒዮና ወቅት ከዚህ ብሔራዊ ቡድን በመመልመል በማሳተፉ የሚያገኛቸው ልዩ ልዩ ጥቅሞች፣ አትሌቶቹን ያፈሩ ክለቦች ስለአትሌቶቹ ሁኔታ የሚያሳውቅበት አሠራር አለመኖሩ እና በአፈሩአቸው አትሌቶች ላይ ያላቸው መብት በግልጽ ተቀምጦ አለመከበሩ በክለቦች ላይ ከፍተኛ የሆነ ቅሬታ እየፈጠረ መሆኑን በናሙና ከተመረጡ ክለቦች በተሰበሰበ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡

124. ከዚህም ሌላ ፌዴሬሽኑ ቅድሚያ ሰጥቶ ሊያከናውነው የሚገባውን ሌሎች የፌዴሬሽኑን የዕለት ተዕለት ሥራዎችን በበቂ ሁኔታ እንዳያከናውን ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል የሚሉ አስተያየቶችም ቀርበዋል፡፡

125. ስለሁኔታው የቴክኒክ ዳይሬክተሩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ላይ ያላቸውን አስተያየት በወቅቱ ለማግኘት ባለመቻሉ የዘገየ እንደሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ ክልሎች ክለቦቻቸውን በጉዳዩ ላይ አማክረው በሚሠጡት መልስ መሠረት ተስተካክሎ እንደሚጠናቀቅ በመውጫያ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል ፡፡

126. ክለቦችን በአግባቡ ለማደራጀት፣ ለመከታተል እና ድጋፍ ለማድረግ የሚያግዝ አንድ ወጥ የሆነ መመሪያ አለመኖር ክለቦች በአግባቡ ተደራጅተው ለአትሌቲክስ ስፖርቱ እድገት ያቅማቸውን ያህል አስተዋጽኦ እንዳያደርጉ በተለይም ተተኪ አትሌቶችን በብቃት እና በብዛት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማፍራ እንዳይችሉ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ የክለቦቹን እንቅስቃሴ በመከታተል የሚከሰቱ የአሠራር ድክመቶችን በወቅቱ ለማረም እና የሚነሱ የመብት ጥያቄዎችን በአግባቡ በማስተናገድ በቅንጅት ውጤታማ ሥራ ለማከናወን አያስችልም፡፡

## II. በፌዴሬሽኑ የአትሌቲክስ ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ፣ አጠባበቅ፣ አጠቃቀምና ልውውጥ አጥጋቢ እና አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ

### ፌዴሬሽኑን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ በተመለከተ

127. ፌዴሬሽኑን የሚመለከቱ ማናቸውም መረጃዎች በተሟላ እና ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ ተደራጅተው በዳታ ቤዝ መያዝ አለባቸው፡፡

128. ፌዴሬሽኑ በአትሌቲክስ ዙሪያ ሊይዛቸው የሚገቡ መረጃዎች በማንዋል እንጂ በዳታ ቤዝ ተይዘው እንዲቀመጡ አልተደረገም፡፡ በማንዋል የተያዘውም ቢሆን

የመረጃ አያያዙ ግልጽ እና መረጃውን በተፈለገ ወቅት ለማግኘት በሚያስችል መልኩ አልተቀመጠም፡፡ የአስተዳደር እና ፋይናንስ ዳይሬክተሯ ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ በዳታ ቤዝም ሆነ በማንዋል ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ መልኩ መረጃዎችን የሚያደራጅ የባለሙያ እጥረት በመኖሩ ችግሩ መከሰቱን ገልጸዋል፡፡

129. በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ (IAAF) የአሰልጣኝነት ኮርስ የወሰዱ አሰልጣኞች ዝርዝር እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተያያዥ መረጃዎች ተጠናቅረው ሊያዙ ይገባል፡፡ ለአሠልጣኝነት የሚያበቃ ሥልጠና የወሰዱ ባለሙያዎች ብዛት እና የወሰዱትን የሥልጠና አይነት የሚያሳይ መረጃ በዝርዝር ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡ ስለሁኔታው የአስተዳደር እና ፋይናንስ ዳይሬክተሯ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመረጃ አያያዝ እና ልውውጥ ስርዓት ላይ ድክመት ስላለ የአትሌቲክስ ክንውንን የሚመለከቱ መረጃዎች ከፌዴሬሽኑ የቴክኒክ ክፍል መዝገብ ቤትን ጨምሮ ለሌሎች የፌዴሬሽኑ የሥራ ክፍሎች አይሠራጭም፡፡ በመሆኑም መረጃው መዝገብ ቤት ስለማይደርስ በተቀናጀ ሁኔታ ተጠናቅሮ ሊያዝ ያልቻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

130. ፌዴሬሽኑን የሚመለከቱ ማናቸውም መረጃዎች ወቅታዊ እና ዘመናዊ መንገድን በተከተለ እና በተፈለጉ ጊዜ ለማግኘት በሚቻልበት ሁኔታ አለመቀመጣቸው አትሌቱም ሆነ ህብረተሰቡ የሚፈልጉትን መረጃ በወቅቱ ለማግኘት እንዳይችሉ በማድረግ ፌዴሬሽኑ የተጣለበትን ኃላፊነት እና ተግባር በተፈለገው ደረጃ ለመወጣት እንዳይችል ያደርገዋል፡፡

## አትሌቲክስን የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎችን ለተጠቃሚ አካላት ማሠራጨትን በተመለከተ፤

131. የሀገሪቱን የአትሌቲክስ ሁኔታ የሚመለከት ወቅታዊ መረጃ ለተጠቃሚዎች በመረጃ መረብ፣ በመጽሔትና በበራሪ ወረቀቶች ሊሰራጩ እንዲሁም የፌዴሬሽኑ የመረጃ መረብም አግባብ ባለው የጊዜ ገደብ ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

132. የአገራችን አትሌቶች ሊያውቋቸው የሚገቡ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው የአትሌቲክሰ ስፖርት ደንቦችና መመሪያዎች የሚያስተዋውቅ መጽሔት እስከ ጥር 30/2000 ዓ.ም እንደሚዘጋጅ በእቅድ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም በዕቅድ

ክንውን ሪፖርት ላይ ተግባራዊ ስለመሆኑ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል ፌዴሬሽኑ ውድድሮችን በሚያዘጋጅበት ወቅት ደረጃውን የጠበቀ በአተሌቲክሱ ዙሪያ ያሉትን ወቅታዊ ሁኔታዎች የሚገልጽ መጽሔት የሚዘጋጅ መሆኑን ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም ከውድድር ውጪ ወጥነት ባለው ሁኔታ መጽሄቱ አይዘጋጅም፡፡ ስለሁኔታው የአስተዳደር እና ፋይናንስ ዳይሬክተሯ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ይህ ሊሆን የቻለው በባለሙያ እጥረት፣ በአቅም እና በቦታ እጥረት እንደሆነ እና ለወደፊት አዲስ ወደተሠራው የፌዴሬሽኑ ህንፃ ዝውውር ሲደረግ እነዚህ ችግሮች ይቃለላሉ የሚል ዕምነት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

133. በዓለም አቀፉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን  የአትሌቲክስ ውድድርን እና ስልጠናን የሚመለከቱ በየጊዜው  የሚወጡ አዳዲስ ደንቦችና መመሪያዎች ለአትሌቲክሱ ማኀበረሰብ በተለይም ለአትሌቶች ተደራሽ በሆነ ሁኔታ የሚሰራጩበት ሁኔታ አለመመቻቸቱ አትሌቲክስን በተመለከተ የተሻለ እና ወቅታዊ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው እና ከአትሌቲክሱ እድገት ጋር እኩል እንዳይራመዱ ያደርጋል፡፡

## III. የአትሌቲክስ ስፖርትን በብቃት ለማከናወን እንዲቻል በፌዴሬሽኑ የሚከናወኑ የአቅም ግንባታ እንቅስቃሴዎች አጥጋቢነትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ

### የአትሌቲክ ማሰልጠኛ ማዕከላት ግንባታን እና አስፈላጊው ቁሳቁስ መሟላትን በተመለከተ፤

134. የወጣቶች የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከላት ተገንብተው በአስፈላጊው የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ተሟልተው ሥራ መጀመር አለባቸው፡፡

135. የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋትና ተተኪ ወጣቶችን ለማፍራት ፌዴሬሽኑ ባደረገው የብር 2,800,000 (ሁለት ሚሊየን ስምንት መቶ ሺህ) ድጋፍ በአራት ክልሎች የተጀመሩ የወጣቶች የአትሌቲክስ ማሠልጠኛ ማዕከላት የግንባታ ሥራዎች በታቀደላቸው ወቅት ያልተጠናቀቁ ሲሆን፣ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችም ያልተሟሉላቸው መሆኑን በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም አንድ ወጥ የሆነ የአትሌቲክስ ማሠልጠኛ መመሪያ ያልተዘጋጀላቸው ሲሆን፣ የአትሌቲክስ ሥልጠና መስጫ መሣሪያዎች ለምሳሌ የመሠናክል እንጨቶች እጥረት መኖር የስፖርቱ ሥልጠና በተፈለገው ጥራት እንዳይሰጥ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

136. የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የሚከናወኑ የግንባታ ሥራዎች በታቀደላቸው ጊዜ ካልተጠናቀቁ እና የሚፈለጉ ቁሳቁሶች ተሟልተው ስልጠና ካልተሰጠ ተተኪ አትሌቶችን በተፈለገው መጠን እና ፍጥነት ለማፍራት አያስችልም፡፡

137. በአራት ክልሎች እየተገነቡ ከሚገኙት የወጣቶች የአትሌቲክስ ማሠልጠኛ ማዕከላት ውስጥ፤ የበቆጂ ማዕከል የተሠራበት ቦታ ረግራጋማ እና የፈሳሽ ማስወገጃ ችግር ያለበት መሆኑን፣ የሀገረ ሠላም የማሰልጠኛ ማዕከሉ ያለበትና ስልጠና የሚሠጥበት ቦታ የተራራቀ፤ በሁሉም ማዕከላት የወንድ እና የሴት አትሌቶች ማደሪያ የተራራቀ አለመሆን እና በአንድ ህንጻ ላይ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህን የመሳሰሉ ችግሮች እያሉ የተወሰኑ የወጣት ማሰልጠኛ ማዕከላት አትሌቶችን በማስገባት ሥልጠና የጀመሩበት ሁኔታ ይታያል፡፡

138. ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ማዕከላቱን በኃላፊነት የሚያስተዳድሩት ክልሎች መሆናቸውን እና ፌዴሬሽኑ ለማዕከላቱ ማስገንቢያ እና የውስጥ ቁሳቁስ ማሟያ የገንዘብ ድጋፍ ብቻ የሚያደርግ መሆኑን የገለጹ ሲሆን፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ መንግስት ለአትሌቲክስ ስፖርቱ ትኩረት ሣይሠጥ መቆየቱ ተጽዕኖ ያሳደረ መሆኑን እና በቅንጅት ማሠልጠኛ ማዕከላቱን ለሚፈለገው አገልግሎት አመቺ በሆነ ሁኔታ በወቅቱ ለማመቻቸት አለመቻሉን ጠቅሰው፤ ወደፊት ከሚመለከታቸው የክልል መንግስት አካላት ጋር በመነጋገር የወጣቶች የአትሌቲክስ ማሠልጠኛ ማዕከላትን በተመለከተ እየታዩ ያሉ ችግሮቹን ለመፍታት ጥረት እንደሚደረግ አስረድተዋል ፡፡

139. እነዚህ ማዕከላት አገልግሎት ለመስጠት በሚያመች ቦታዎች ላይ አለመመሥረታቸው እና አሠራራቸው እና አደረጃጀታቸው በተገቢ ጥናት ተደግፎ አለመከናወኑ በወጣት ሠልጣኞቹ ላይ ችግር ሊያስከትሉ ከመቻላቸውም በላይ የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት አያስችልም፡፡

## የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በተመለከተ፤

140. ፌዴሬሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን እንዲስፋፉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በየክልሉ በተቋቋሙ የወጣት ማሠልጠኛ ማዕከላትም ሆነ የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች አካባቢ በተፈጥሮ የተገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ሜዳዎች ያሉ ቢሆንም እነዚህ የተፈጥሮ ሜዳዎች ለአትሌቲክስ ስፖርቱ በሚያስፈልግ መልኩ ማለትም የተለያዩ የአትሌቲክስ ዘርፎችን (events) ለማሰልጠንም ሆነ ለመሰልጠን በሚያመች ሁኔታ ተስተካክለው የተዘጋጁ አይደሉም፡፡ ይህን ችግር ለማቃለል ከባለ ሀብቶች ወይም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመሥራት ሁኔታ ትኩረት አልተሰጠውም፡፡

141. ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ይህ ተግባር ሠፊና ከፍተኛ መዋለ ንዋይ የሚያስፈልገው ከመሆኑ አንፃር የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር የሥራ ድርሻ እንደሆነ እና ፌዴሬሽኑ የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ለማስፋፋት ስልት (Strategy) መቅረጽ እንደማይጠበቅበት፤ ከፌዴሬሽኑ አቅም በላይ በመሆኑም ሚኒስቴሩ ባለሀብቶችን በማስተባበር እና በማሳተፍ ሊያቃልል የሚገባው ተግባር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

142. የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ የተቋቋመበት ዋነኛ አላማ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የሚቻልበትን ሁኔታዎች ለማመቻቸት እንደመሆኑ መጠን ለሌላ አካል የሚያስተላልፈው እና የሚተወው ተግባር ሊኖር አይገባም፡፡ ለአትሌቲክስ ስፖርት አመቺ የሆኑ ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ማመቻቸት ካልተቻለ እና በወጣት ማሠልጠኛ ማዕከላትም ሆነ በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች የታቀፉት ብቻ ሳይሆን ሌላውም ኅብረተሰብ ሊጠቀምባቸው የሚችልባቸው የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ በቅርበት አለመገኘት ኅብረተሰቡ በአትሌቲክስ ስፖርቱ የተሻለ ተሳትፎ እንዳያደርግ፣ በአዕምሮ፣ በአካል እና በስነ-ልቦና የተሻለ በመሆን ለሀገሪቷ ሁለንተናዊ እድገት የተሻለ አስተዋጽኦ እንዳያበረክት ከማድረጉም በላይ ብቁ እና ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት የሚደረገውን ጥረት ውጤታማነት ይጎዳዋል፡፡

## ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ መንደር ግንባታን በተመለከተ፤

143. ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ መንደር ተገንብቶ በከፍተኛ ደረጃ አትሌቶች ሊሠለጥኑበት ይገባል፡፡ ዓለም አቀፍ ደረጃን በጠበቀ ሁኔታ ሊገነባ የታሠበው የሠንዳፋ አትሌቲክስ መንደር ሥራን ለማስጀመር 1,743,147.00 (አንድ ሚሊየን ሰባት መቶ አርባ ሶስት ሺህ አንድ መቶ አርባ ሰባት ብር) የተመደበ ቢሆንም አጥር ከማጠር ውጪ ምንም እንቅስቃሴ አልተደረገም፤ የግንባታ ሥራውን እስከ ሰኔ 30 ቀን 2000 ዓ.ም ለማስጀመር ዕቅድ ቢያዝም በተያዘለት ዕቅድ መሠረት ለመከናወኑ ወይም ላለመከናወኑ በዕቅድ ክንውን ሪፖርት ላይ አልተገለፀም፡፡

144. ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የአትሌቲክስ መንደር አለመገንባቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚደረጉ ውድድሮች አትሌቶች ደረጃውን የጠበቀ እና ሳይንሳዊ መንገድን የተከተለ ሥልጠና በማግኘት በስነልቦናም ሆነ በብቃት የተሟሉ ሆነው እንዳይገኙ እና የተለየ ተሰጥኦ ያላቸው አትሌቶች በብዛት ለማፍራት እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## የአዲስ አበባ ስታዲየም የመሮጫ ትራክ አጠቃቀምን በተመለከተ፤

145. በሀገሪቱ በብቸኝነት የሚገኝ ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የአዲስ አበባ ስታዲየም የመሮጫ ትራክ ለብሔራዊ አትሌትነት የተመረጡት አትሌቶች የሚሠለጥኑበት እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረጉ ውድድሮች ለመወዳደሪያነት ብቻ እያገለገለ ይገኛል፡፡ በተለያዩ ክለቦች የታቀፉ አትሌቶቸ ትራክ ላይ ልምምድ ባለማድረጋቸው በትራክ ላይ በሚደረጉ የተለያዩ ውድድሮች ላይ ሲሳተፉ አዲስ በመሆን ግር መሠኘት የሚያጋጥማቸው መሆኑን በናሙና በተደረገ ጥናት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ትራክ የሚሰጠው አገልግሎት አነስተኛና ውስን ቢሆንም አገልግሎት መስጠት በጀመረ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጎዳት እና የመሳሳት ሁኔታ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ይታይበታል፡፡

146. ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ የልማት ፕሮጀክት ኤክስፐርት ተጠይቀው በሰጡት መልስ ትራኩ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረጉ ውድድሮች ብቸኛ የማወዳደሪያ ቦታ እና አላቂ በመሆኑ ጫና ከበዛበት በአጭር ጊዜ እንዳያልቅ በማሰብ ገደብ የተጣለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ እና ፕሬዝዳንት ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ የአትሌቲክስ ማዘውተሪያ ቦታዎችን ማስፋፋት በይበልጥ የሚመለከተው የወጣቶች እና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴርን ሲሆን፣ በተለያዩ ምክንያቶች ይህን ተግባር የሚፈለገውን ያህል ለማከናወን ባለመቻሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚያገለግል አንድ የመሮጫ ትራክ ብቻ መኖሩን፤ ይህንኑ ትራክ በቁጠባ የመጠቀም ኃላፊነት የፌዴሬሽኑ ቢሆንም በተለያዩ ሀገራዊ እና ሃይማኖታዊ በዓላት እንዲሁም የዘፈን ዝግጅቶች ምክንያት የመሮጫ ትራኩ በከፍተኛ ሁኔታ እየተጎዳ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

147. በተለያዩ ክለቦች የታቀፉ አትሌቶች በትራክ ላይ ልምምድ ባለማድረጋቸው በተለያዩ ውድድሮች ላይ ሲሳተፉ አዲስ መሆን እና ግር መሠኘት እያጋጠማቸው ባለበት ሁኔታ ትራኩ ከተሠራበት ዓላማ ውጪ በሆኑ የተለያዩ ዝግጅቶች ምክንያት በከፍተኛ ሁኔታ እየተጎዳ መሆኑ ለታለመለት ተግባር አገልግሎት ሳይሰጥ ከጥቅም ውጭ እንዲሆን እያደረገው ይገኛል፡፡

## የማሻሻያ ሀሳቦች

### የአትሌቲክስ ስፖርትን በኃላፊነት የሚያንቀሳቅሱ አካላት አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሠራርን በተመለከተ፤

148. ፌዴሬሽኑ የሌሎች ሀገራት ልምዶችን ጭምር በማገናዘብ የሀገሪቱ ዜጎች በየደረጃው ከስፖርቱ የሚገኘውን ሁለንተናዊ ጥቅም ማግኘት እንዲችሉ በማድረግ ሀገሪቷ የተሻለ ተጠቃሚ እንድትሆን ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ታችኛው የሀገሪቱ መዋቅር ድረስ ግልጽ የሆነ የሥራ ድርሻ እንዲኖር እና ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ስለ አትሌቲክስ ስፖርት አስተዳደር ተገቢውን ግንዛቤ በየጊዜው እንዲያገኙ በማድረግ ቅንጅታዊ በሆነ ሁኔታ ለመሥራት የሚችሉበት አደረጃጀት እና የአሠራር ሥርዓት እዲፈጠር ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

### የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የሚያስፈልጉ ደንቦችና መመሪያዎችን በተመለከተ፤

149. ፌዴሬሽኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን መረጃዎች መሠረት በማድረግ የሀገሪቷን ሁኔታ ያገናዘቡ ወቅታዊ የአትሌቲክስ ደንቦች፣ ህጐችና መመሪያዎች በጥናት ሊዘጋጅና በየጊዜው ወቅታዊነታቸው እየተጠበቀ እንዲሻሻሉ ሊያደርግ የሚገባ ሲሆን፣ በራሱም ሆነ በአይ.ኤ.ኤ.ኤፍ (IAAF) በየጊዜው የሚዘጋጁ ሌሎች የተለያዩ ወቅታዊ መረጃዎች (documents) የአትሌቲክስ ስፖርቱን ለሚያንቀሳቅሱ እና ከፌዴራል ጀምሮ በየደረጃው ለሚገኙ አግባብነት ላላቸው አካላት አቅም በፈቀደው መጠን በየጊዜው የሚደርሱበት የአሠራር ስልት ሊቀየስ ይገባል፡፡

### የፋይናንስ ድጋፍ ማሰባሰብን በተመለከተ፤

150. ገቢ ያስገኛሉ ተብሎ የሚያዙ እቅዶች ሲዘጋጁ የሀገሪቱን የዘመን አቆጣጠር በአገናዘበ ሁኔታ እንዲከናወን ሊደረግ ይገባል፡፡

151. ፌዴሬሽኑ ኅብረተሰቡ በተለይም ባለ ሀብቶች ስለ አትሌቲክስ ስፖርቱ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ የተለያየ ድጋፍ እንዲያደርጉ እና ስፖርቱን በተሻለ ሁኔታ ለማስፋፋት የሚያስችል የገንዘብም ሆነ የሞራል

ድጋፍ ለማግኘት እንዲችል የረጅም እና የአጭር ጊዜ ዕቅድ በማዘጋጀት ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡

152. ለአትሌቲክስ ስፖርት እድገት ከወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስቴር በተጨማሪ የትምህርት ሚኒስቴር እና የክልል ትምህርት እና ስፖርት ቢሮዎች እንዲሁም የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተሻለ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

153. ለሰንዳፉ አትሌቲክስ መንደር ግንባታ የተሻለ ሥራ ሊሠራ የሚችል ብቃት ያለው የገቢ አሠባሣቢ ኮሚቴ በማቋቋም የተጀመሩ የገቢ ማሰባሰብ ሥራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

## <u>ዝቅተኛ ተሳትፎ እና ውጤት የሚታይባቸው የአትሌቲክስ ስፖርት ውድድር መስኮችን በተመለከተ</u>

154. ፌዴሬሽኑ ዝቅተኛ ተሳትፎ እና ውጤት በሚታይባቸው የአትሌቲክስ ስፖርት አይነቶቸ ዙሪያ ጥናት በማካሄድ ለነዚህ የአትሌቲክስ አይነቶች የሚሆኑ ሥልጠና እና የውድድር መሣሪያዎች በየደረጃው ሊሟሉ የሚችሉበትን ስልት በመቀየስ እና በነዚህ በአትሌቲክስ ዘርፎች የተሻለ የውድድር ዕድል በማመቻቸት አትሌቶች እንዲበረታቱ እና ፍላጐቱ ኖሯቸው እንዲሠሩ በማድረግ የተሻለ ውጤት እንዲገኝ ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

## <u>በብሔራዊ አትሌትነት የሚታቀፉ አትሌቶች ምርጫን በተመለከተ፣</u>

155. ሀገርን ወክለው የሚወዳደሩ ብቃት ያላቸውን አትሌቶች ለማፍራት በብሔራዊ አትሌትነት የሚታቀፉ አትሌቶችን በአግባቡ ለመምረጥ የሚያስችል ቋሚ መመዘኛ መስፈርት በመስኩ ባለሙያዎች ወጥነት ባለው ሁኔታ ተጠንቶ ሊዘጋጅ እና እንደአስፈላጊነቱ እየተሻሻለ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

156. ክለቦች አትሌቶቻቸውን በብቃት ማሰልጠን የሚችሉባቸው ሁኔታዎች እንዲመቻችላቸው ድጋፍ በማድረግ ውድድሮቹ ከመከናወናቸው በፊት ቀደም ብሎ ሀገሪቱን በመወከል በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የሚሣተፉ አትሌቶች ብቃትን ብቻ መሠረት ባደረገ ሁኔታ በመመልመል ለውድድር አዘጋጅቶ ይዞ መቅረብ ወይም ፌዴሬሽኑ ብሔራዊ ቡድን በማቋቋም እና አመቱን ሙሉ

በጀት መድቦ ካሰለጠናቸው አትሌቶች መካከል ሀገሪቱን ወክለው የሚወዳደሩን መለየት ከሚሉት አማራጮች መካከል አዋጪ የሆነውን በጥናት በመለየት ከክለቦች ጋር እየታየ ያለውን አለመግባባት ለማቃለል እና የተሻለ ውጤት ለማምጣት ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

## ሀገሪቱን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶች ምርጫን በተመለከተ

157. ሀገሪቱን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶች ለመምረጥ የሚያስችል መስፈርት ብቃት ባላቸው የዘርፉ ባለሙያዎች ሊዘጋጁ፤ በባለድርሻ አካላት ውይይት ተደርጉባቸው እና ሊካተቱ የሚገባቸው ተቀባይነት ያገኙ ሃሳቦች ከተካተቱ በኋላ በሚመለከተው አካል ጸድቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

158. በአትሌቶች የጤንነት ብቃት ዙሪያ ሚዛናዊ እና ተቀባይነት ያለው አስተያየት ለመስጠት እንዲቻል የአትሌቶችን የጤንነት ብቃት የሚያረጋግጥ የጤና ባለሙያዎች ቡድን እንዲደራጅ ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

## ብሔራዊ ቡድኑን የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞች ምርጫን በተመለከተ

159. ብሔራዊ የአትሌቲክስ ቡድኑን የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መስፈርት ሊቀመጥና ምርጫውም በመስፈርቱ መሠረት ሊከናወን ይገባል፡፡

160. ፌዴሬሽኑ የሚፈልጋቸውን የሥራ መደቦች በጥናት በመለየት ለሁሉም የተለዩ የሥራ መደቦች መስፈርቶችን በማስቀመጥ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት የአሰልጣኞች ምልመላ ሊከናወን ይገባል፡፡ ለየሥራ መደቦቹ በተዘጋጁት መስፈርቶች መሠረት አሰልጣኞችን ለመመደብ ካልተቻለ እና ተጨማሪ ወይም ሊቀየር የሚገባ የሥራ መደብ ካስፈለገ ሁኔታው ተጠንቶ በቅድሚያ ተስተካክሎ እና በሚመለከተው አካል ፀድቆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

## የአሠልጣኝነት እና የዳኝነት ኮርሶች ሥልጠና የሚሰጡ አሰልጣኞች እና ሰልጣኞችን በተመለከተ፤

161. ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ብቃት ያላቸውን የአትሌቲክስ የአሰልጣኝነትና የዳኝነት ኮርስ ስልጠና የሚሰጡ አሰልጣኞች እና ሰልጣኞችን ለመለየት

የሚያስችል ተገቢ መስፈርት በጥናት በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊደረግ እና ግልጽና ተጠያቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት ሊቀየስ ይገባል፡፡

162. ብቃት ያላቸውን የአትሌቲክስ አሠልጣኞች እና ዳኞች በማፍራት ስፖርቱን በብቃት ለማስፋፋት በፌዴሬሽኑ የተዘጋጀው የሠልጣኞች መምረጫ መስፈርት በሚመለከተው የበላይ አካል እንዲጸድቅ ሊደረግ፤ በዚህ በጸደቀው የሠልጣኞች መምረጫ መስፈርት መሠረት ሠልጣኞች በቅድሚያ ሊመረጡ እና ስልጠናውን በአግባቡ መከታተላቸውን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

## <u>በአሰልጣኝነትና የዳኝነት ኮርስ ስልጠና ላይ የሚካፈሉ ሠልጣኞች ብዛትን በተመለከተ፤</u>

163. በፌዴሬሽኑ ተዘጋጅተው የሚሰጡ የአሰልጣኝነትና የዳኝነት ኮርስ ስልጠናዎች ሆነ ሌሎች ተመሳሳይ ሥልጠናዎች በአንድ አሰልጣኝ የሚሰጥ ሥልጠናን እንዲከታተሉ በስታንዳርድ የተቀመጠውን የሠልጣኞች ብዛት ጠብቆ እንዲከናወን ሊደረግ ይገባል፡፡

## <u>ለሠልጣኞች የሚሰጥ ፈተና ዝግጅትና ግምገማን በተመለከተ፤</u>

164. በፌዴሬሽኑ ተዘጋጅተው በየትኛውም ደረጃ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ፈተና ገለልተኛ በሆነ አካል አንድ ወጥ በሆነ መልኩ እንዲዘጋጅ እና እንዲገመገም ማድረጉ ሠልጣኞች ከተሰጣቸው ሥልጠና ሊያገኙት የሚገባውን ዕውቀት በአግባቡ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፣ ሠልጣኞችን በእኩል ደረጃ ለመመዘን እና የሚሰጠውም ሰርተፊኬት ሚዛናዊ እንዲሆን ለማድረግ ያስችላል፡፡

## <u>*የአሠልጣኝነት እና የዳኝነት ስልጠና ሥርዐተ ትምህርት ዝግጅትን* በተመለከተ፤</u>

165. የአሠልጣኝነት እና የዳኝነት ሥልጠናም ሆነ ሌሎች አትሌቲክስ ነክ ሥልጠናዎችን ለመስጠት ከሀገሪቱ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ወጥ የሆነ የስልጠና ሥርዓተ ትምህርት (curriculum) ከIAAF የስልጠና ሥርዓት ጋር በማገናዘብ ሊዘጋጅና በሚመለከተው አካል ፀድቆ ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡

## የስልጠና ማቴሪያል ዝግጅትን በተመለከተ፤

166. የስልጠና አሠጣጡ አንድ ወጥ በሆነ መልኩ እንዲከናወኑ እና ሰልጣኞቹም ከሥልጠና በኋላ የተፈለገውን የአሠልጣኝነት እና የዳኝነት ስልጠና ክህሎት በብቃት እንዲያገኙ እና ከሥልጠና በኋላ የስልጠና ማቴሪያሎቹን በማንበብ ግንዛቤአቸውን ለማስፋት እንዲችሉ የዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን (IAAF) የስልጠና መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ እና ከሀገሪቷ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ አንድ ወጥ የሆኑ የስልጠና ማቴሪያሎች ሊዘጋጁና በሥልጠና ወቅት ለሥልጠና ተሳታፊዎች ሊሰጡ ይገባል፡፡

## የስልጠና መርሐ ግብር ዝግጅትን በተመለከተ፤

167. ፌዴሬሽኑ የስልጠና መርሐ ግብር ከማዘጋጀቱ በፊት በሥልጠናው እንዲሳተፉ የሚጠበቁ ክልሎች እና ክለቦች በቅድሚያ የሥልጠና ፍላጎታቸውን የሚያሳውቁበት አሠራር በመዘርጋት ፍላጎታቸው በመርሐ ግብሩ ዝግጅት ውስጥ እንዲካተት ማድረግ እና ሥልጠና የሚሰጥበትን ወቅት በቅድሚያ እንዲያውቁት በማድረግ ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ሊያደርጉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

## በፌዴሬሽኑ ስር አትሌቶችን የሚያሠለጥኑ አሠልጣኞችን ግምገማን በተመለከተ

168. በፌዴሬሽኑ በየደረጃው ተተኪንም ሆነ ነባር አትሌቶችን የሚያሠለጥኑ አሠልጣኞች ሥራቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ለማረጋገጥ በየጊዜው የሚገመገሙበት ሥርዐት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

## የአትሌቲክስ ስፖርት አሠልጣኝነት የሙያ ፈቃድ ደረጃን በተመለከተ

169. ፌዴሬሽኑ ትኩረት እና ቅድሚያ ሠጥቶ በአትሌቲክስ አሠልጣኝነት ላይ ለሚሠማሩ ባለሙያዎች ደረጃ ሊያወጣ እና በደረጃው መሠረት ፈቃድ በመስጠት ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ እና አትሌቶች ብቃት ባላቸው አሠልጣኞች ሊሠለጥኑ የሚችሉበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

## ውድድር ማካሄጃ መሳሪያዎችን በተመለከተ፤

170. የአትሌቲክስ ውድድር ማካሄጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀምና አያያዝ የሚያውቅ ባለሙያ ፌዴሬሽኑ ሊያፈራ እና አስፈላጊ በሆኑ ውድድሮች ላይ ለመጠቀም የሚቻልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

## የታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክት አቀራረጽን በተመለከተ፤

171. የታዳጊ ወጣቶች ማሰልጠኛ ኘሮጀክት ጣቢያዎች በጥናት ላይ በመመርኮዝ ለስፖርቱ ተስማሚ የሆኑ አካባቢዎች ለመለየት የሚያስችል ተገቢ የመምረጫ መስፈርት ተዘጋጅቶ ሊመሠረቱ እና ወደፊት በሌሎች ኘሮጀክቶቹ ባልተቋቋሙባቸው ክልሎች ሊቋቋሙ የሚችሉበት ሁኔታ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## በታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክቶች ላይ የሚደረግ ክትትልና ግምገማን በተመለከተ፤

172. ከፌዴራል ጀምሮ በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊነት ያለባቸው ባለድርሻ አካላት በታዳጊ ወጣቶች የአትሌቲክስ ኘሮጀክት ጣቢያዎች ላይ በየጊዜው ማድረግ የሚገባቸውን ክትትልና ግምገማ በአግባቡ እንዲያከናውኑ የማስተባበር ተግባርን ፌዴሬሽኑ ትኩረት ሰጥቶ ሊያከናውነው ይገባል፡፡ ፌዴሬሽኑ በታዳጊ ወጣቶች የአትሌቲክስ ኘሮጀክት ጣቢያዎች ላይ ያከናወነው የግምገማ ሪፖርት በወቅቱ ለኘሮጀክት ጣቢያዎች እንዲደርሳቸው ሊደረግ ይገባል፡፡

173. ከፌዴራል ጀምሮ በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ለአትሌቲክስ ስፖርቱ ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጡ ተገቢ የግንዛቤ ሥራ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ሊሰጥ የሚችልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

## ለታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክት የሚደረግ ድጋፍን በተመለከተ፤

174. በፕሮጀክት ለታቀፉ ታዳጊ ወጣቶች የሚደረገው የትጥቅም ሆነ የገንዘብ ድጋፍ በወቅቱ እንዲደርስ ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

## በታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክት የሚታቀፉ ታዳጊ ወጣቶች አመራረጥን በተመለከተ፤

175. በአትሌቲክስ ፕሮጀክት ጣቢያዎቹ የሚታቀፉት ታዳጊ ወጣቶች በትክክል ለመምረጫ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የተመረጡ መሆኑን፣ የምልመላ ሥርዓትንና ደንብን በመከተል አግባብነት ያላቸው ታዳጊዎች በፕሮጄክቱ መታቀፋቸውን ፌዴሬሽኑ በየጊዜው ክትትል ማድረግ እና ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

176. የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚከናወን እስከሆነ ድረስ ታዳጊ ወጣቶቹ እድሚያቸው 14 ሲሞላ በየዓመቱ የሚታቀፉበት እና በየደረጃው ከዕድሜ እኩዮቻቸው ጋር ልምምድም ሆነ ሥልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

## በታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክት የታቀፉ ታዳጊ ሰልጣኞች ከኘሮጀክቱ የሚለቁበትን ጊዜ በተመለከተ፤

177. በአትሌቲክስ ፕሮጀክቶች የታቀፉ ታዳጊ ሠልጣኞች ዕድሜያቸው ከ17 ዓመት በላይ ሲሆን ከኘሮጀክት እንዲለቁ የኘሮጀክት ጣቢያው ኃላፊም ሆነ በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊነት ያለባቸው ባለድርሻ አካላት በቅርበት ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

## የታዳጊ ሠልጣኞች የስልጠና ጊዜን በተመለከተ፤

178. የታዳጊ አትሌቲክስ ኘሮጀክት አሠልጣኞች የሥልጠና መርሐ ግብራቸውን ከማውጣታቸው በፊት በፕሮጀክቱ የታቀፉ ሠልጣኞች የቀለም ትምህርት የጊዜ ሠሌዳ እና የስልጠና የጊዜ ሠሌዳ በማገናዘብ እና በማስማማት የተመቻቸ ቀን እና ሰዓት ሊያዝላቸው ይገባል፡፡

## የታዳጊ ወጣቶች ስልጠና አሰጣጥ መመሪያን በተመለከተ፤

179. ፌዴሬሽኑ የዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ለታዳጊ ወጣቶች የአሌቲክስ ስልጠና ያዘጋጃቸውን መመሪያዎች ባገናዘበ ሁኔታ ቀደም ያሉ ተሞክሮዎችን፣ ዖታና እድሜን እንዲሁም ተሠጥኦን መሠረት ያደረገ መመሪያ በማዘጋጀት እና ለፕሮጀክቶቹ እንዲደርስ በማድረግ በፕሮጀክት የታቀፉ ታዳጊ ወጣቶች

የሚሠጠው አትሌቲክስ ሥልጠና ይህንኑ መመሪያ መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲከናወን ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

## ለታዳጊ የአትሌቲክስ ሰልጣኞች መሰጠት ያለበትን የሕክምና አገልግሎት በተመለከተ፤

180. ከሥልጠናው ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥማቸው ጉዳት ለታዳጊ የአትሌቲክስ ፕሮጀክት ሠልጣኞች ተገቢውን የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ለፕሮጀክቶቹ ተገቢውን ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነቱን ሊወጣ እንዲሁም ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ተገቢው ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

## በታዳጊ አትሌቶች ውድድር ላይ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ፤

181. በተለያየ ደረጃ በሚከናወኑ የታዳጊ ወጣቶች አትሌቲክስ ስፖርት ውድድሮች በፕሮጀክቱ የታቀፉ ታዳጊዎች ብቻ የሚሳተፉበት እንዲሆን ዕድሜን በተመለከተ ጥብቅና ጠንከር ያለ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ስልት በጥናት ሊቀየስ እና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡

## አትሌት ማናጀሮች ፈቃድ አሠጣጥ እና ክትትልን በተመከተ

182. የአትሌት ማናጀሮችን፣ የአትሌቶችን፣ የክለቦችን እና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን መብት እና ግዴታ በአግባቡ ያገናዘበ ግልጽና የተሟላ የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ወጥቶ በሚመለከተው አካል ጸድቆ ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡

## በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ የሴቶች ተሳትፎን በተመለከተ፤

183. ፌዴሬሽኑ በአትሌቲክሱ ዘርፍ የሴቶች ተሳትፎ በየደረጃው ሊጠናከር እና ሊያድግ የሚችልበትን ሁኔታ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ሊከታተለው እና ሴቶች የተሻለ ተሳትፎ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

184. ፌዴሬሽኑ በአትሌቲክስ ስፖርት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ያለውን የጎላ ሚና ኅብረተሰቡ እንዲገነዘብ እና ሴቶች ልጆቹን ተሳታፊ ከማድረግም በዘለለ ሴቶችን

በዚህ መስክ ለማበረታታት የሚጠበቅበትን ሌሎች ተግባራት እንዲያከናውን ተገቢ የቅስቀሳ ተግባር ሊያከናውን ይገባል፡፡

## የጸረ ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ ስምምነትን ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ

185. ፌዴሬሽኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የፀረ ዶፒንግ ምርመራ በሀገር ውስጥ ውድድሮች ላይ ዘላቂነት ባለው መልኩ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

## በውጭ ሀገራት በግል ውድድር ለማድረግ የሚጠይቁ አትሌቶች ፈቃድ አሠጣጥን በተመለከተ

186. አትሌቱ ጥሪውን ያገኘው በተለያዩ ፌዴሬሽኑ ባዘጋጃቸው ውድድሮች ያስመዘገበውን ሰዓት መሠረት በማድረግ ፌዴሬሽኑ ወይም ጥሪውን ያደረገው ሕጋዊ አካል እንደ ዝቅተኛ መስፈርት ያስቀመጠውን መመዘኛ አሟልቶ እና ጥሪን ያገኘው ሕጋዊ መንገድን በመከተል ሕጋዊ ከሆነ አካል ከሆነ አትሌቱ ዕድሉን ሊጠቀምበት እንዲችል መመሪያው ታይቶ ቢሻሻል አትሌቶች ህገወጥ መንገድን እንደአማራጭ እንዳይወስዱ በማድረግ አትሌቶቹም ሆነ ሀገሪቷን ተጠቃሚ ሊያደርግ ስለሚችል ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

187. አትሌቶች በግል ላገኙት የውድድር ዕድል ፍቃድ ለመጠየቅ በሚመጡበት ጊዜ የት የት መሄድ እና መስተናገድ እንዳለባቸው የሚያሣይ የሥራ ሂደት (Flow chart) እንዲሁም በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ተስተናግደው እንደሚጨርሱ የሚገልጽ የጊዜ ገደብ የሚያሳይ ግልጽ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ ተጠቃሚዎች በግልጽ ሊያዩት በሚችሉበት ቦታ እንዲቀመጥ ሊደረግ ይገባል፡፡

188. በብሔራዊ አትሌት የታቀፉ አትሌቶችን ያፈሩ ክለቦች አትሌቶቹ በሚያደርጉአቸው ውድድሮች ላይ ሊኖራቸው ስለሚገቡ መብቶች በግልጽ ሊቀመጡ እና በእነዚህ አትሌቶች ላይ የሚወስነውን ውሣኔ የሚያውቁበት አሠራር ሊዘረጋ እና ሊያመቻች ይገባል፡፡

## ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌላቸው አትሌቶች በሀገር ውስጥ ልምምድ እንዲያደርጉ ፈቃድ መስጠትን በተመለከተ፤

189. ሀገሪቱ ለአትሌቲክስ ካላት ተፈላጊ መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ንብርት አንፃር የአትሌቲክስ ስፖርት ከስፖርትነቱ ባለፈ ለሀገሪቱ እንደ አንድ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ማግኛ ለመሆን ያለውን አጋጣሚ እና ዕድል ለመጠቀም ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

## ክሶች እና አቤቱታዎችን ገለልተኛ በሆነ አካል ማስተናገድን በተመለከተ፤

190. ፌዴሬሽኑ ከፌዴራል ጀምሮ በየደረጃው የሚገኙ አትሌቶች በአትሌቲክሱ ዘርፍ በተሳትፎ በሚቆዩባቸው ወቅቶች መብትና ግዴታቸውን ሊገነዘቡ የሚችሉበት እንዲሁም ቅሬታ ሲኖራቸው ቅሬታቸው አግባብነት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ እንዴት ማቅረብ እና መግለጽ እንዳለባቸው ቀጣይነት ባለው መልኩ በቂ ግንዛቤ ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡ ከአትሌቲክስ ስፖርት ጋር የተያያዙ ክሶችና አቤቱታዎች በሚኖሩበት ጊዜ ክሶችና ቅሬታዎችን የሚያይ ገለልተኛ የቅሬታ ሰሚ አካል እንዲኖር ቢደረግ ችግሩን በተሻለ ሁኔታ ለማቃለል ያስችላል፡፡

## የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦችን አደረጃጀት የሚመለከት መመሪያ ማዘጋጀትን በተመለከተ

191. ፌዴሬሽኑ የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦችን ለማደራጀት እና ለመከታተል እንዲቻል የተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንዲጸድቅ በማድረግ በሥራ ላይ እንዲውል አስፈላጊውን ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

## ፌዴሬሽኑን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ በተመለከተ

192. የፌዴሬሽኑን እንቅስቃሴም ሆነ ሌሎች አትሌቲክስን የሚመለከቱ መረጃዎች ለአጠቃቀም በሚያመች ሁኔታ ወቅታዊና ኮምፒዩተራይዝድ በሆነ መልኩ ተደራጅተው ሊያዙና መረጃዎቹን ማግኘት የሚገባቸው ተጠቃሚዎች በቀላሉ ሊያገኟቸው በሚችሉበት ሁኔታ ማስቀመጥ ይገባል፡፡

## አትሌቲክስን የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎችን ለተጠቃሚ አካላት ማሠራጨትን በተመለከተ፤

193. አትሌቲክስ ስፖርትን የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎች የያዙ መጽሔቶች እና በራሪ ወረቀቶች ውድድር ሲኖር ብቻ ሳይሆን በቋሚነት በየተወሰነ ጊዜያት ተዘጋጅተው ለተጠቃሚው ሊሰራጩ የሚችሉበት እንዲሁም የፌዴሬሽኑን የመረጃ መረብ በመጠቀም አትሌቲክስን የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎች በየጊዜው የሚሠራጩበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

## የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከላት ግንባታ እና በአስፈላጊው ቁሳቁስ መሟላትን በተመለከተ

194. ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት የወጣቶች የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከላት በተቻለ መጠን በታቀደላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ እና በሚያስፈልጋቸው ቁሳቁሶች፣ የሠው ኃይል ወዘተ… ተሟዕልተው ሥራቸውን በብቃት ለመጀመር እንዲችሉ አስፈላጊው ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

195. በወጣት ሠልጣኞቹ ላይ የተለያዩ አካላዊ እና የስነ ልቦና ችግር የሚያስከትሉ ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት የወጣት ማሠልጠኛ ማዕከላቱ አሠራር እና አደረጃጀት ሊጠናና ሊስተካከሉ የሚገባቸው ሁኔታዎቾ ከወዲሁ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡

## የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን በተመለከተ፤

196. ፌዴሬሽኑ አቅም በፈቀደ መጠን በወጣት ማሠልጠኛ ማዕከላትም ሆነ በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች የታቀፉትን ጨምሮ ኅብረተሰቡ በአጠቃላይ ተስማሚ የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን በቅርበት የሚያገኝበት እና በየትኛውም እድሜ የሚገኙ ዜጎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

## ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ መንደር ግንባታን በተመለከተ፤

197. የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ሁሉ በማስተባበር ዓለም አቀፍ ደረጃን በጠበቀ ሁኔታ ሊገነባ የታሰበው የሰንዳፋ አትሌቲክስ መንደር ግንባታ ሥራ

ሊቀጥል እና በተዘጋጀው የሥራ ዕቅድ መሠረት ሊከናውን የሚችልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ፌዴሬሽኑ አስፈላጊውን ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

## የአዲስ አበባ ስታዲየም የመሮጫ ትራክ አጠቃቀምን በተመለከተ፤

198. የመሮጫ ትራኩ በሀገሪቱ ውስጥ በብቸኝነት የሚያገለግል ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ ትራክ በመሆኑ ለሌሎች ተግባራት እንዲውል በመደረጉ የተፈጠረው ችግር እንዲቃለል እና ለተባለለት ዓላማ ብቻ ሊውል የሚችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ከሚመለከታቸውን አካላት ጋር በማነጋገር ተከታታይ ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

199. በተለያዩ ክለቦች የታቀፉ አትሌቶች ትራኩን አስቀድመው በመለማመድ የተሻለ ዝግጅት እንዲኖራቸው ለማድረግ ስለሚረዳ ትራኩን በማይጎዳ መልኩ ሁኔታው ተጠንቶ በትራኩ ላይ ልምምድ የሚያደርጉበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

# አባሪዎች

## ጠቅላላ ጉባኤው ተሳታፊዎች

- ✓ የየክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተወካዮች፤
- ✓ የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንትና የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላት፤
- ✓ የአትሌት ተወካዮች፤
- ✓ የክልል ክለቦች ተወካይ፤
- ✓ የዳኞችና የአሰልጣኞች ተወካዮች፤
- ✓ የክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ስፖርት ቢሮዎች ተወካዮች፤
- ✓ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር የሚወከል ሙያተኛ፤
- ✓ የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት፤ የቴክኒክ አገልግሎት፤ የአስተዳደርና ፋይናንስ፤ የህዝብ ግንኙነት ላፊዎች
- ✓ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጡ የክብር አባላትና
- ✓ በጉባኤው የተሰየመ ኦዲተር ናቸው፡፡

# አባሪ ሁለት

## የኦዲት መስፈርቶች (evaluative criteria)

1.1.1 በሁሉም ክልሎች የአትሌቲክስ ስፖርትን በኃላፊነት የሚያንቀሳቅሱ አካላትን እንዲቋቋሙ እና እንዲደራጁ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.1.2 የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት የሚያስፈልጉ ደንቦች፣ መመሪያዎች ወዘተ በጥናት ሊዘጋጁና በየጊዜው ወቅታዊነታቸው እየተጠበቀ በየደረጃው ለሚገኙ አግባብነት ላላቸው አካላት ሊሰራጩ ይገባል፡፡

1.1.3 ፌዴሬሽኑ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት ተገቢ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልት ነድፎ ሊንቀሳቀስ ይገባዋል፡፡

1.2.1 የወጣቶች የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከላት ተገንብተው በአስፈላጊው የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ተሟልተው ሥራ መጀመር አለባቸው፡፡

1.2.2 ፌዴሬሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን እንዲስፋፉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

1.2.3 ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ መንደር ተገንብቶ በከፍተኛ ደረጃ አትሌቶች ሊሠለጥኑበት ይገባል፡፡

1.2.4 በአትሌቲክስ ስፖርት ተሳትፎ ዝቅተኛ ውጤት የሚታይባቸውን የውድድር መስኮች ለማሻሻል ትኩረት ሊሠጠው ይገባል፡፡

1.2.5 የአሠልጣኝነትና የዳኝነት ስልጠና ኮርስ የሚሰጡ አሰልጣኞች ለመምረጥ የሚያገለግል ግልጽ የሆነ መስፈርት ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡

1.2.6 ለአሰልጣኝነትና የዳኝነት ኮርስ ተሳታፊዎች ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የመምረጫ መስፈርት መኖር አለበት

1.2.7 የአሰልጣኝነትም ሆነ ለዳኝነት ሠልጣኞች የሚያዘጋጅ ፈተናን የሚያዘጋጅና ፈተናውን የሚገመግም ገለልተኛ አካል /ባለሙያ/ ሊኖር ይገባል፡፡

1.2.8 ፌዴሬሽኑ በአትሌቲክስ ስፖርት የሴቶች ተሳትፎ የሚጠናከርበትን እና የሚያድግበትን ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

1.2.9 ሀገርን ወክለው ለሚወዳደሩ ብሔራዊ አትሌቶች ለልምምድ የሚያስፈልጋቸው ቁሳቁሶች እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ግብዓቶች መሟላት አለባቸው፡፡

1.2.10 የአሠልጣኝነትም ሆነ የዳኝነት ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓተ ትምህርት (curriculum) ተቀርጾ ተግባራዊ ሊደረግና በየጊዜው እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያ ሊደረግበት ይገባል፡፡

1.2.11 የአሠልጣኝነት እና የዳኝነት ስልጠና ለመስጠት የሚያገለገል የሥልጠና ማቴሪያል ተዘጋጅቶ በሥልጠና ወቅት ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡

1.2.12 የአሠልጣኝነት ስልጠና ለመስጠት መርሃ ግብር ከመውጣቱ በፊት የክልሎችንና የክለቦች ፍላጐት ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡

1.2.13 በአትሌቲክስ ስፖርት በአሠልጣኝነት የሚሰማሩ ባለሙያዎች ፌዴሬሽኑ

የሙያ ደረጃ ሊያወጣና የአሰልጣኝነት ፈቃድ በሚመጥኑት ደረጃ ሊሠጥ ይገባል፡፡

1.2.14 ታዳጊ ወጣቶችን በአትሌቲክስ ስፖርት ለማሠልጠን የሚቀረጹ ኘሮጀክቶች ጥናት ላይ በመመርኮዝ ሊቀርጹና በየክልሉ ሊተገበሩ ይገባል፡፡

2.1 በየክልሉ የሚካሄዱ የታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክቶች ላይ በየዓመቱ ክትትልና ግምገማ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.2 በታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክት የሚታቀፉትን ታዳጊ ወጣቶች ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.3 በታዳጊ ወጣቶች አትሌቲክስ ፕሮጀክቶች የታቀፉ ታዳጊ ሠልጣኞች ዕድሜያቸው 17 ዓመት በላይ ሲሆን ከኘሮጀክት መልቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡

2.4 በታዳጊ ወጣቶች አትሌቲክስ ፕሮጀክት የታቀፉ ሠልጣኞች የስልጠና የጊዜ ሠሌዳና የቀለም ትምህርት የጊዜ ሠሌዳ ተጣጥሞ መቀናጀት አለበት፡፡

2.5 ለአንድ የታዳጊ ኘሮጀክት ቢያንስ አንድ አሠልጣኝና አንድ ረዳት አሠልጣኝ ሊኖር ይገባል፡፡

2.6 የታዳጊዎች አትሌቲክስ ሥልጠና ለመስጠት ጾታን፣ ዕድሜንና ተሠጥኦን መሠረት ያደረገ የሥልጠና መመሪያ ሊዘጋጅ እና በዚህ መመሪያ መሠረት ሥልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

2.7 ፌዴሬሽኑ በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት ውድድር ወቅት በፕሮጀክት የታቀፉት ታዳጊዎች ብቻ የሚሳተፉበት እንዲሆን ተገቢውን ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

2.8 ለታዳጊ ሠልጣኞች ከሥልጠናው ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥማቸው ጉዳት የህክምና አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

2.9 ሀገርን ወክለው በተለያዩ አህጉር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የሚወዳደሩ አትሌቶችን ለማፍራት በብሔራዊ አትሌትነት የሚታቀፉ አትሌቶችን መምረጫ ግልጽ የሆነ መስፈርት ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡

2.10 ሀገሪቱን በመወከል በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የሚሣተፉ አትሌቶች ብቻ በብሔራዊ አትሌት ቡድን ውስጥ ሊታቀፉ ይገባል፡፡

2.11 ሀገሪቱን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶች ለመምረጥ የሚያገለግል ግልጽ የሆነ መስፈርት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

2.12 በየውድድር ዘርፉ የብሔራዊ ቡድን አትሌቶችን እና አገርን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶችን የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መስፈርት ሊኖር እና በመስፈርቱ መሠረት ምርጫው ሊከናወን ይገባል፡፡

2.13 ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው የአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ አስፈላጊው የውድድር ማካሄጃ መሣሪያዎችን አሟልቶ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

2.14 ከአትሌቲክስ ስፖርት ጋር የተያያዙ ክሶችንና አቤቱታዎችን የሚሠማ

ከፌዴሬሽኑ መደበኛ ተግባራት ገለልተኛ የሆነ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊቋቋም ይገባል፡፡

2.15 የፀረ ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ ኮንቬንሽን ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው የአገር ውስጥ ውድድሮች ላይ ተግባራዊ የሚያደርግበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

2.16 አትሌቶች በውጭ አገር በግል ውድድር ለማድረግ ሲጠይቁ ፈቃድ የሚሰጥበት ግልጽ የሆነ መመሪያና መስፈርት ሊኖር ይገባል፡፡

2.17 በየደረጃው ተተኪ ንም ሆነ ነባር አትሌቶችን የሚያሠለጥኑ አሠልጣኞች በየሶስት ወሩ የሚገመገሙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ሊገመገሙ ይገባል፡፡

2.18 በዜግነት ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ አትሌቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ልምምድ ማድረግ የሚችሉበት የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት በጥናት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.1 ፌዴሬሽኑን የሚመለከቱ ማናቸውም መረጃዎች በተሟላ እና ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ ተደራጅተው በዳታ ቤዝ መያዝ አለባቸው፡፡

3.2 በሀገሪቱ እየተንቀሳቀሱ ያሉት የአትሌት ማናጀሮች ፈቃድ ለመስጠትና ሁኔታውን ለመከታተል የሚያስችል ተገቢ ደንብ ሊዘጋጅ፤ የአትሌት ማናጀሮችም በተዘጋጀው ደንብ መሠረት ፈቃድ ሊያወጡ እና ፈቃዳቸውንም በየዓመቱ ሊያሳድሱ ይገባል፡፡

3.3 የሀገሪቱን የአትሌቲክስ ሁኔታ የሚመለከት ወቅታዊ መረጃ ለተጠቃሚዎች በመረጃ መረብ፣ በመጽሔትና በበራሪ ወረቀቶች ሊሰራጩ እንዲሁም የፌዴሬሽኑ የመረጃ መረብም በየሳምንቱ ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.4 በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ (IAAF) የአሰልጣኝነት ኮርስ የወሰዱ አሰልጣኞች ዝርዝር እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተያያዥመረጃዎች ተጠናቅረው ሊያዙ ይገባል፡፡

3.5 ፌዴሬሽኑ የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦች እንዲደራጁ ለማድረግ የሚረዳ መመሪያ ማውጣትና ተፈፃሚነቱን መከታተል አለበት፡፡